# ስፌት ተኮር ትምእርታዊ ጉዳዮች ትንተና በደቡብ ወሎ ዞን የተመረጡ ወረዳዎች

ብርሃኑ ቦጋለ ተስፋዬ[1]


**አጠቃሎ**

የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በተመረጡ የደቡብ ወሎ ወረዳዎች ያለውን የስፌት ትምእርታዊ ጉዳዮችን መመርመር ነው። መረጃዎች ከቀዳማይ እና ከካልዓይ ምንጮች በተለያዩ ዘዴዎች ተሰብስበው ተሰብስበዋል። ዓይነታዊ የምርምር ስልትን በመከተል የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ፤ የፍሮይድ የአዕምሮ መዋቅራዊ ሞዴል የሆኑትን የስብዕና መዋቅሮች ማብራሪያ ሞዴሎች አኳያ በመፈተሽ፤ በይዘት ትንተና እና በትርጓሜ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። በትንታኔው መሰረት የጥናቱ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚስተዋሉት የስፌት ተግባራት ትዕምርታቸው በፍካሬና በእማሬ የሚገለጽ ሲሆን፣ ሙያ፣ ሙያተኛ፣ ግብዓቶች፣ መሥሪያዎች እና ምርቶች ጋር መመሰያዎቹ የተያያዙ ናቸው። የመመሰያዎቹ አወካከልም ምስስሎሻዊ (resemblance)፣ ስምምነታዊ (symbolic) እና ምክንያታዊ (index) እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። ከስፌት ጋር ግንኙነት ያላቸው የፍካሬ ልቦና ጉዳዮች ሁለት መልክ ያላቸው ሲሆን፣ እነሱም የፍሮይድ የሰብዕና መዋቅሮች እና መንስኤዎች ናቸው። በኢድ የሰብዕና መዋቅር ሥነሕይወታዊ ጉዳዮች ሲጠቀሱ፣ በኢጎ ደግሞ ሥነልቦናዊ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ። እንዲሁም በልዕለ ኢጎ ማኅበረ-ባህላዊ እና ግብረገባዊ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ። ከስፌት ጋር በተያያዘ የተስተዋሉት ሥነቃላዊ ጉዳዮች ስር የክልከላ ንግግሮች፣ ፈሊጦች፣ ቃል ግጥሞች እና ተረኮች ሲጠቀሱ፣ ይዘታቸውም ከሙያዎቹ፣ ከሙያተኛው፣ ከግብዓት፣ ከመሥሪያ መሣሪያ፣ ከምርቶቹ ምንነት፣ ከተግባርና አጠቃቀም አውድ ጋር የተያያዙ ትዕምርታዊ ጉዳዮችን ማንጸባረቂያ መሆናቸውን ጥናቱ አመልክቷል። በጥናቱ የተስተዋሉ አዎንታዊ ግኝቶችን ሊያስቀጥሉ የሚችሉ፣ ከስፌት ጋር የተያያዙ ለውጦች፣ ቀጣይነቶች እና ጾታ ተኮር ጉዳዮችን በስፋትና በጥልቀት ጥናት ቢደረግ የሚሉ ምክረሃሳቦች በአጥኚው ተሰንዝረዋል።


**ቁልፍ ቃላት**፤ [ስፌት፣ ትዕምርት፣ አወካከል፣ ሰብዕና]

[1] የአጥኚው የኢሜል አድራሻ bbrish99@gmail.com ሲሆን፣ በወሎ ዩኒቨርሲቲ በማኅበራዊና ሰብዓዊ ሳይንስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል መምህር እና በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪ ሲሆን፣ ስልክ ቁጥር + 251912256505. የጥናቱ ዋና አማካሪ ዶር. መሐመድ ዓሊ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)፣ ዶር. አጸደ ተፈራ (ከወሎ ዩኒቨርሲቲ)።

## 1. *መግቢያ*

የእደጥበብ ሥራ ከፎክሎር ዘርፎች በቁሳዊ ባህል ጥናት መስክ የሚጠና ሲሆን፣ መሰረታዊ እሳቤው ከጠቀሜታዊ እሴት ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ሲባል የሰው ልጅ በእለት ተዕለት ሕይወቱ የሚፈልገውን አገልግሎት እና መሰረታዊ ፍላጎቱን የሚያሟሉ አስፈላጊ ቁሶችን ለማዘጋጀት በሚል እሳቤ የሚከውነው ሙያ ነው። ስለሆነም የሸመና፣ የወስፌ ስፌት፣ የሸክላ፣ የእንጨት እውቀት፣ ክህሎት እና ተፈጥሯዊ ከሆነ "ሞድ" (Design) ብቃትን ተጠቅሞ ለጥቅም የሚውል ነው። በዚህም እንደ ቅርጫት (ስፌት) ያሉ እቃ ለመያዥነትና ለማጓጓዣነት፣ ሸመና ለዕለት ተዕለት ልብስነት፣ የእንጨት ሥራ ለቤት ቁሳቁስነት ሲባል ይመረታሉ (Moses[1] 2014:8)። የቅርጫት ሥራ፣ ሸመና፣ የብረት ሥራ እና የሸክላ ሥራ በቀደምት እና በመሰረታዊነት በዕደ ጥበብ ስር የሚጠቀሱ ናቸው (Sellschop, Golgblat & Hemp 2005:3)። በዚህም ሙያው እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከትና እነዚህን ለመሥራት እውቀታዊ፣ ጥበባዊና ክህሎታዊ ጉዳዮችን የሚጠይቅ ተግባር ነው።

እደጥበብ በሌላ አገላለጽ "የተግባር ጥበብ" (wisdom of practice) በሚል ይገለጻል (Leinhardt 1990:18)። ይህም የተግባር ጥበብነቱ የህሊናና የአካል ውህደትን በማሳየት ረገድ ከውስጣዊ እና ከውጫዊ አኳያ ያለውን መስተጋብር የሚያመለክት ሲሆን፣ ከጥበባዊ ጽንሰ ሃሳብ ያለፈ፣ የእውቀት ማሳያ፣ ለመፍጠር ተግባራዊነትን የሚጠይቅ እንቅስቃሴ ነው (Shanks & McGuire 1996:82)። ከማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ እውቀታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ምህዳራዊ ጉዳዮች ጋር የማገናኛ ኃይል ነው (Buszek 2011)። በተያያዘም በሙያው ውጤቶች አማካይነት የአንድን ማኅበረሰብ የሥራ ኃይል፣ ግብ፣ እምነት፣ አመለካከት፣ እሴት፣ ትዝታ፣ ራዕይ፣ ታሪክ እና ወግ በመግለጽ ረገድ ሁነኛ ፋይዳ አለው (Johnson 2010)።

በተለያዩ ተሞክሮዎች (ግላዊና አካዳሚያዊ) ለማስተዋል እንደቻልኩት በወስፌ ስፌት ትምእርታዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ፣ በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ዘንድ ተወስኖ በስፋትና በጥልቀት የተሰራ ወይም የቀረበ የምርምር ሥራ አላጋጠመኝም። በዚህ ረገድ አንድ ጥናታዊ መጣጥፍ ማለትም፤ Ahmed (1999) የሚጠቀስ ሲሆን፣ መሰረታዊ ትኩረቱም በሐረር አካባቢ ያለውን የወስፌ ስፌት ሙያ እና ምርቶች ላይ ያለውን ፋይዳ መተንተን ነው። እንዲሁም የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም በጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም ላይ "ጥቅምት የማርና የስፌት ወር" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው አውደ ርዕይ ላይ በተሳተፍኩበት ወቅት ባህላዊ የስፌት ምርቶች በሂደት በምዕራቡ ዓለም ሸቀጦች እየተለወጡ እንደሆነ የሚገልጽ በራሪ ወረቀት አዘጋጅቶ ነበር። ይህም አንዱ ለጥናቱ መነሻ የሆነ ጉዳይ ነው።

---

[1] በዚህ ጥናት ውስጥ የሚገኘው የዘመን አቆጣጠር የተገለጸው በአማርኛ የተጻፉ መጻሕፍት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ሲሆን፣ በእንግሊዝኛ የተፃፉት ግን በጎርጎርሳውያን መሠረት ነው። እንዲሁም የምንጮች አጻጻፍና አጠቃቀስ መሰረት ያደረገው የAPA (2010) (6$^{th}$ ed.). ስልትን ነው። ለጥናቱ የመጻፊያ ፎንት፤ ለአማርኛ Nyala ሲሆን፣ ለእንግሊዘኛ ደግሞ Time New Roman ጥቅም ላይ ውሏል።

የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በደቡብ ወሎ ዞን የተመረጡ ወረዳዎች ያለውን ስፌት[2] ተኮር ትምእርታዊ ጉዳዮችን መመርመር ነው። የጥናቱ ጥያቄዎች የስፌት መመሰያዎች ምንድን ናቸው? የትምእርታዊ ጉዳዮች አወካከል ስልቶች ምን ዓይነት ናቸው? ከትምእርቶቹ ጋር የተያያዙ የፍካሬ ልቦና ጉዳዮች እንዴት ይገለጻሉ? የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት ለመፈተሽ የታለመ ነው።

ጥናቱ ስለስፌት፣ በአጠቃላይ ስለእደጥበብ ሥራ ጽንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮች ለፎክሎር፣ ተዛማጅ መስኮች ተማሪዎች እና ተመራማሪዎች ግንዛቤ ይሰጣል። በስፌት ዙሪያ ለሚደረጉ ምርምሮች መነሻ ይሆናል፤ በዚህ ረገድ ያለውን ክፍተት ይሞላል። ባህልን የመጠበቅና የመመርመር ተልዕኮ ላላቸው መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስፌት ስራዎች እንዲጠበቁና እንዲጠኑ ያግዛል።

የጥናቱ ቦታዎች በደቡብ ወሎ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ቃሉ፣ ኮምቦልቻ እና ቦረና ሲሆኑ፣ ታላሚ የንሞና ዘዴን መሰረት በማድረግ ተመርጠዋል። የጥናቱ ዓይነት ዓይነታዊ ሲሆን፣ አተያዮቹ ደግሞ ኢትኖግራፊያዊ ነው። የመረጃ አቀባዮች የናሙና አወሳሰድ በማኅበረሰቡ ዘንድ የተሻለ ግንዛቤ እና ቅርበት ያላቸው አካላት በታላሚ (purposive) እና በውስጠ አዋቂ ጥቆማ (snowball sampling) የንሞና ዘዴዎች መሰረት በማድረግ ተመርጠዋል። በተጨማሪም በምቹ ሁኔታ መረጃዎችን ለማግኘት ተግዳሮት ሲኖር አመች የናሙና (convenience sampling) ስልት ተግባራዊ ሆኗል።

ቀዳማይ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት እና ሰነድ ፍተሻ ተሰብስበዋል። ካልዓይ መረጃዎች የጥናቱን ክፍተት ለማሳየትና ለማናበቢያነት በክለሳ ድርሳንና በጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ክፍል ጥቅም ላይ ውለዋል። መረጃዎቹም ከውስጣዊና ውጫዊ እይታ አንጻር (Emic and Ethic Perspective) ተተንትነዋል። እንዲሁም የመረጃ አቀራረቡ በገለጻ፣ በትንተና እና በትርጓሜ ስልቶች ላይ የተመሰረተ ነው። የሥነትምእርት ንድፈ ሃሳብ እና የፍሮይድ የሰብዕና መዋቅር ሞዴሎች በጥናቱ ለመተንተኛነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

ፎክሎር በሥራቸው ሌሎች ክፍሎችን የያዙ አራት ዘርፎች አሉት (Dorson 1972)። ከዚህ ውስጥ የቁሳዊ ባህል አላባ ሆኖ Dorson ከዘረዘራቸው አምስት ዓይነቶች መካከል ጥናቱ በእጅ ጥበብ ላይ የተወሰነ ሲሆን፣ ይህም ከሚመለከታቸው መካከል በዋናነት በስፌት ላይ የተወሰነ ነው። ጥናቱ ስፌት ተኮር ትምእርታዊ ጉዳዮችን መመርመር ላይ የተወሰነ ነው።

---

[2] ስፌት የሚለው ቃል የያዘው ገለጻ በሦስት አግባብ ሲገለጽ ይስተዋላል። ለምሳሌ፤ (1) የመስፋት ስራ ወይም ሙያ፤ (2) ልብስ፣ ጫማ ወዘተ. በመርፌና በክር የተያያዘበት ቦታ፣ (3) እንደ መሶብ፣ ሙዳይ፣ ሰፌድ የመሰለውና ብዙውን ጊዜ ከስንደዶ፣ ከአክርማ፣ ከግራምጣ ወዘተ. የሚዘጋጅ የቤት እቃ በሚል ይገለጻል። በዚህ ጥናት አውድ መሰረት ስፌት የሚለው ቃል ጽንሰ ሃሳብ በዋናነት በተራ ቁጥር 1 እና 3 ላይ የተገለጸውን የሚመለከት ሲሆን፣ በጥናቱም “የወስፌ ስፌት” የሚል ገለጻ ጥቅም ላይ ውሏል (አማርኛ መዝገበ ቃላት [አመቃ]፣ 1993፣ ገጽ 127)።

በደቡብ ወሎ አካባቢ በተለይ የአማሬ ቁና[3] እና ሚግራ ጉራ ጭቁርሳ (የስንደዶና አክርማ ቀጨታ ወይም ለቀማ) የሚሉ ገለጻዎችን መስማት የተለመደ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ማኅበረ ባህላዊ እና አካባቢያዊ ጠቃሽ ወይም መለያ በመሆናቸው በጉዳዩ ላይ እና በአካባቢዎቹ ላይ ጥናት ለማድረግ መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው። በዚህም የወስፌ ስፌት ባለሙያዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ ቢሆንም፣ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሦስቱ ወረዳዎች ላይ ብቻ ነው።

የጥናት ስፍራዎቹ ከአየር ንብረት አኳያ ቆላ እና ደጋ የሚወክሉ መሆናቸው ሌላው የምርጫ ሰበብ ነው። ለዚህም "ደገኛ ሰፊ ነው፣ ቆለኛ ፈታይ ነው" (ንግግር 2)[4] የሚለው ገለጻ በማሳያነት ሊወሰድ የሚችል ነው። በተጨማሪም በአካባቢው የሙከራ ጥናት (Pilot Study) በተደረገበት ጊዜ የጥናት ስፍራዎቹ በአንጻራዊነት ከሌሎቹ የተሻለ የወስፌ ስፌት ባለሙያዎች የሚገኙባቸው በመሆኑ፣ ለጥናቱ ካላቸው ግብ መቺነት እና ምቹነት አኳያ ሊመረጡ ችለዋል።

በጥናቱ የተካተቱት ተጠኚዎች በዋናነት የወስፌ ስፌት ባለሙያዎች ሲሆኑ፣ ከሙያው ጋር ግንኙነት ያላቸው ለአብነት፤ በወስፌ ስፌት ምርቶች ንግድ ላይ ያሉ፣ ተጠቃሚዎች እና የባህል አዎቂዎችና ባለሙያዎች በጥናቱ ተካተዋል። በዚህ ጥናት በዋናነት በእድሜ የገፉ እና ለረጅም ጊዜ በወስፌ ስፌት ሙያ ዙሪያ ያሉና የቆዩ 35 ያህል ወንድና ሴት መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል።

## 2. ጽንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል ሁለት ጉዳዮች የተነሱ ሲሆን፣ እነዚህም ጽንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ ናቸው። በጽንሰ ሃሳብ ስር የስፌት፣ የቅርጫት ስፌትና የወስፌ ስፌት ነጥቦች ቀርበዋል። በንድፈ ሃሳበዊ ፈርጅ ደግሞ ትምእርታዊ ጉዳዮችና የመረጃ መተንተኛ ሞዴሎች ቀርበዋል።

### 2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ሦስት ነጥቦች የቀረቡ ሲሆን፣ እነሱም ስፌት፣ የቅርጫት እና የወስፌ ስፌት ናቸው።

#### 2.1.1 ስፌት

ስፌት በአመዛኙ ከሁለት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ፍቺ ሲሰጠው ይስተዋላል። ይኸውም ከሙያው፣ ከግብዓቱ እና ከምርቱ ጋር ነው። በዚህም ስፌት፤ የመስፋት ሥራ ወይም ሙያ፤ እንዲሁም እንደመሶብ፣ ሙዳይ፣ ሰፌድ የመሳሰሉ ብዙውን ጊዜ ከስንደዶ፣ አክርማ፣ ሰበዝ፣ ግራምጣ የሚዘጋጅ የቤት እቃ የሚል ፍቺ አለው (አመቃ፣ 1993፣ 127)። በተያያዘም ስፌት የሚለው ቃል

---

[3] የአማሬ ቁና እንዲህ እንደዛሬው ዘመናዊ የዳኝነት ስርዓት ባልተሰፋፋበት ወቅት በተለይ የከላላ እና የጃማ አካባቢ ህዝቦች በጋራ ይዳኙበት የነበረ እና አሁንም ያለ ማኅበራዊ ስምምነት ነው (ድንግል ውበት፣ 2011)።

[4] በጥናቱ በዚህ መልክ የቀረቡ ገለጻዎች ንግግሮቹ ወይም የሥነ ቃል ቅርጾቹ በጥናቱ የአባሪ ክፍል የሚገኙበትን የቁጥር ተራ የሚያመለክት ሲሆን፣ በዚህ ገለጻም የሥነ ቃል ቅርጾቹ ምንጭ እና የምንጩ ዓይነት የተገለጸበት ነው።

በእንግሊዝኛው "Weaving" በሚል የሚገለጽ ሲሆን፣ ከሙያ፣ ከምርት፣ ከስልት፣ ከግብዓት እና ከመሥሪያ መሣሪያ ጋር በተቆራኘ መልኩ ሲጠቀስ ይስተዋላል (Hebbar 2015:2)።

ከሙያ አኳያ ያለውን ብያኔ ስፌት ሁለት ሙያዎችን አካቶ የያዘ ሲሆን፣ እነሱም የቅርጫት ሥራ (basket weaving) እና የሽመና ሥራ (textile weaving) ናቸው (Hebbar 2015:2)። የቅርጫት ሥራ ቅርጻዊ ጥንካሬ ያላቸውን (structurally stable baskets) ሲመለከት፣ የሽመና ደግሞ ጎናዊ ቅርጽ እና የተጣጣፊነት (non structural form) መገለጫ ያላቸውን የሚመለከት ነው።

እነዚህ የስፌት ዓይነቶች በቅርጽ፣ በግብዓት እና በአሠራር ስልት ልዩነት ያላቸው ቢሆንም፣ አንድ የሚያደርጋቸው አላባ (element) አላቸው። ከአላባዎቹ መካከል የመሥሪያ ግብዓቶች "ተለማጭነት" (flexibility) እና "ጥንካሬ" (rigid) በቀዳሚነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

የግብዓት ጥንካሬ በቅርጫት ሥራ ላይ ጎልቶ መስተዋሉ ከሽመና ሥራ አኳያ ልዩ የሚያደርጋቸው መገለጫ ነው። እነዚህ ግብዓቶች በዋናነት ሁለት መልክ ያላቸው ሲሆን፣ ስያሜያቸው እንደ ሙያዎቹ ዓይነት ልዩነት አለው። ከቅርጫት ሥራ አኳያ መሰበዣ ግብዓት (warp element) እና መስፊያ ግብዓት (weft element) በሚል ሲገለጹ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ድር (warp riser) እና ማግ (warp sinker) ከሽመና አኳያ የሚጠቀሱ ናቸው (Osei-Poku & Osei 2014)።

የስፌት ጥበብ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ሁለት መሰረታዊ አላባዎችን እርስ በርሳቸው በማጠላለፍ ስርዓት ታላሚ ምርት ለመፍጠር የሚከናወን ስልት ሲሆን፣ ምርቶችን ለመሥራት ቀላል መሳሪያዎችን (simple tools) ይጠቀማል። ስፌት ተፈጥሮአዊ የሆነ መነሻ ያለው ሲሆን፣ የሸረሪት ድር እና የወፍ ጎጆ በማሳያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። እነዚህ የአሰራር ስልቶች ከቅርጻዊ ምስስሎሽ ባለፈ ለአገልግሎት ፍላጎት በቀዳሚነት መዋላቸው ሌላው አምሳያ መገለጫቸው ነው (Hebbar 2015:2)።

#### 2.1.1.1 የቅርጫት ስፌት

የቅርጫት ሥራ በዋናነት አገልግሎታዊ እሳቤን መሰረት በማድረግ፣ ርዝመታዊ እና ቅርጻዊ ጥንካሬ ያላቸውን አካባቢያዊ ግብዓቶችን በማጠላለፍ እና በማጣበቅ የሚከወን አንዱ የስፌት ዓይነት ነው (Hebbar 2015:6)። በዚህ ተግባርና ዓላማ መነሻነት የሚገኘው ምርት *ቅርጫት* ይባላል።

የቅርጫት ስራ ምርቶች ከሰው ልጅ ህይወት ጋር ቁርኝት አላቸው። ይህ ቁርኝትም በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ዘንድ እንደሚጠቀስ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Osei-Poku & Osei 2014:12)። ለዚህም በተለይ ከመሶብ የስፌት ምርት ጋር በተያያዘ ቀጥሎ የቀረበውን የሐዲስ ኪዳን፤ የማቴዎስ ወንጌል ገለጻ ማስተዋል ይቻላል።

> ...ኢየሱስም፡- እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም አላቸው። እነርሱም፡- ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሳ በቀር በዚህ የለንም አሉት። እርሱም፡- እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ አላቸው። ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ። አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሳ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፣ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፣ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ። *ሁሉም በልተው ጠገቡ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሱ።* ከሴቶችና ከልጆችም በቀር የበሉት አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር (ምዕራፍ 14፣ ከቁጥር 16-21)።

የቅርጫት ምርት ለመያዣነት መዋል አንዱ ተግባር ነው። በታሪክ እነዚህ ምርቶች የተለያዩ ሸቀጦችን ለመያዣነት እና ለማጓጓዣነት ጥቅም ላይ መዋላቸው ምርቶቹ እንዲታወቁና እንዲስፋፉ መነሻ መሆኑን ምንጮች ይጠቁማሉ (Osei-Poku & Osei 2014፡2)።

የቅርጫት *ሥራ* ምርቶች የተለያዩ ናቸው። የተግባርና የግብዓት ዓይነት መለያየት ለምርቶቹ ዓይነት መነሻ ጉዳይ ነው። በዚህም የመ*ሥሪያ* ግብዓቱ እንደሚገኝበት ስፍራ መነሻነት ምርቶቹ የራሳቸው የሆነ ልዩ መገለጫ ሊኖራቸው ይችላል። ለዚህ ማሳያው ከመስክ በተገኘው መረጃ መነሻነት ስንደዶ እና አክርማ የደጋውን አካባቢ ሲወክሉ፣ የወንጋ ግብዓት ደግሞ የቆላውን አካባቢ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። ከዚህ በተያያዘም ከሙያ አኳያ “ደገኛ ሰፌ ነው፣ ቆለኛ ፈታይ ነው” (ንግግር 2)[5] የሚለው ገለጻ ከዚህ አኳያ ሊታይ የሚችል ነው።

የቅርጫት *ሥራ* ዓይነቶች ባላቸው ውቅር (pattern) እና የአሰራር ስልት የተለያዩ ናቸው። እነዚህም የወስፌ *ሥራ* (coiled basketry)፣ መሸመን (twined)፣ መጠቅለል (wrapped work)፣ የምንጣፍ *ሥራ* (matting work)፣ መጎንጎን (plaited work) እና የቀርቀሃ *ሥራ* (wicker work) ናቸው (Das 1979:190)። ከነዚህ መካከል የወስፌ *ሥራዎች* በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው ናቸው።



ምስል 1. የወስፌ *ሥራ* (ምንጭ Making a basic coiled basket- jonsbushcraft.com jonsbushcraft.com)

---

[5] በጥናቱ በዚህ መልክ የቀረቡ ገለጻዎች ንግግሮቹ ወይም የሥነ ቃል ቅርጾቹ በጥናቱ የአባሪ ክፍል የሚገኙበትን የቁጥር ተራ የሚያመለክት ሲሆን፣ በዚህ ገለጻም የሥነ ቃል ቅርጾቹ ምንጭ እና የምንጩ ዓይነት ተገልጾ ይገኛል።

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መካከል የወስፌ ስፌት በኢትዮጵያ፣ ቡርንዲ፣ ሩዋንዳ እና ደቡብ አፍሪካ ታዋቂነት ያለው የአሰራር ስልት ነው (Silva 2004:21)። በተለይም ከወስፌ ስፌት ምርት መካከል ሌማት ወይም "ማእድ" (Ethiopian Coil Food) በአሰራር ብልሃቱና በግብዓቱ ዓይነት ማራኪና ውበት ያለው መሆኑ ተጠቃሽ ነው።

የቅርጫት ሥራ አንዱ የስፌት ዓይነት ሲሆን፣ ተለማጭነት፣ ክብነት እና አካባቢያዊነት አንኳር መገለጫዎቹ ናቸው። የመሥሪያ ግብዓቶቹ በአንጻራዊነት ጠንካራ መሆን እና አለመሆን በወስፌ ሥራዎች መካከል የሚስተዋል ልዩነት ነው።

#### 2.1.1.2 የወስፌ ስፌት

የወስፌ ስፌት ጥንታዊነት ያለው የማምረት ተግባር እና አንዱ የስፌት ዓይነት ነው (Hebbar 2015:17)። እንዲሁም በግብዓት፣ በመሥሪያ መሣሪያ፣ በቅርጹና በአሰራር ሂደቱ ሊገለጽ ይችላል። የወስፌ ስፌት ሥራ ከቅርጽ አኳያ በክብ ንድፍ የሚሰራ ሲሆን፣ የስፌቱን ቅርጽ ሊወስን የሚችለው እና "መነሻ" በመባል የሚታወቀው "መቋጠር" (central core) በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በዚህም ተደጋጋሚ የዙር መጠን በመጨመር የስፌት ቅርጹ እንዲጨምር ይደረጋል።

በዚህ ሂደትም የተለያዩ የስፌት ቅርጻዊ ክፍሎች ይሰራሉ። እያንዳንዱም የስፌት ዙር ከመሥሪያ ግብዓትና ከመስበዣ ግብዓት ጋር በመሥሪያ መሣሪያ (ምሳሌ፤ ወስፌ) አማካይነት እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰፋ ይደረጋል (Silva 2014)። ለስፌት ምርቱ መጠንከር ወይም አለመጠንከር የመስበዣ ግብዓቱ ዓይነት የጎላ ድርሻ አለው። ለዚህም ማሳያው በምርት ሂደት ሰበዝን መጠቀም እና ሰንበሌጥን መጠቀም ልዩነት የጎላ እና ዘርፈ ብዙ ነው። ከነዚህም መካከል የጥንካሬ እና የዋጋ ልዩነት መኖር በዚህ ረገድ ሊጠሱ የሚችሉ ናቸው።

### 2.2 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

#### 2.2.1 የሥነትምእርት ንድፈ ሃሳብ

ትምእርት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በቀዳሚነት በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተነሳው በስዊዘርላንዳዊው Ferdinand de Saussure (1857-1913) በተባለው የመዋቅራዊ ሥነልሳን ምሁር Semiology በሚለው የጥናት ዘርፍ ነው (Martin and Ringham 2000:42)። ትምእርት ጽንሰ ሃሳባዊ ቁስን የሚመለከት ሲሆን፣ ተወካይ (Signifiers) እና እማሬ (Signified) የሚባሉትን ሁለት ጉዳዮች አጣምሮ የያዘ ነው። የመጀመሪያው የተወከለውን ጉዳይ ሲመለከት፣ ሁለተኛው ደግሞ የተሸከመውን ትርጉም ይመለከታል (Whitehead 1985: 8-9)። በዚህ የትርጉም ሂደትም እማሬ (Denotation) እና ፍካሬ (Connotation) የፍች ደረጃዎች የሚነሱ ናቸው (Martin and Ringham 2000:29-42)።

በPeirce አተያይ መሰረት ማንኛውም ትዕምርት የሚፈልቀው የትምእርቱ አካል በሆኑ ሦስት የትምእርት አላባውያን ዙሪያ በሚደረግ ረቂቅ ሂደት አማካይነት ነው (Danesi 2004)። እነዚህም ምልክት (Symbol)፣ ቁስ (Object) እና ትርጓሜ (Interpretant) ናቸው። ይህ ብያኔ የጽሀፈት ቋንቋን መሰረት አድርጎ የቀረበ ነው። ቋንቋ ደግሞ ጽሑፋዊ፣ አልያም ቃላዊ ሊሆን ይችላል። ምልክት አዕምሯዊ ነው፤ ቁስ አካላዊ ነው፤ ትርጓሜ ባህላዊ ነው።

ትምእርቶች በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ። ለምሳሌ፤ ቀለም፣ እንቅስቃሴ፣ ቁስ፣ ድምጽ፣ ነጸብራቅ፣ ሂሳባዊ ቀመር፣ ወዘተ. ሆነው ለተፈጠሩለት ነገር የቆሙ ናቸው (Denesi 2004:5; Berger 2004:4)። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ከቁሳዊ ባህል ጋር በተያያዘ "ቁሳዊ ትምእርት" (Object Signs) በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። ይህ ሁኔታም እንደ Baudrillard ምደባ በአራት ደረጃዎች[6] የሚታይ ሲሆን፣ እነዚህም አገልግሎታዊ፣ ገበያዊ ምክንያት፣ ስጦታዊ እና ክብራዊ ተምሳሌት ናቸው (Woodward 2007:76)።

የጥናት መስኩ በወካይ ተወካይ መካከል ያለውን ግንኙነት ትኩረት ያደረገ ነው። በዚህም ትዕምርቶች ከወካዩ አንጻር ሦስት ስልቶች ያሏቸው ሲሆን፣ እነዚህም አምሳያነት (resemblance)፣ አመክንዮታዊ (index) እና ስምምነታዊ (symbol) ናቸው። በአምሳያነት ቁሱን በማመሳሰል ሲገለጽ ለአብነትም ስዕል እና "ካርቱን" ይጠቀሳሉ። በምክንያታዊነት ወካዩ ነገሩን በአካላዊ ገጽታ ባለው ግንኙነት ሲገለጽ ለአብነትም እሳትና ጭስ ይጠቀሳሉ። በማመሳሰል ወካዩ በጊዜ ሂደት በሚፈጠር ዘልማዳዊ ስምምነት አማካይነት የሚከሰት ነው። ለዚህም ፊደላት እና ሥርዓተነጥቦች ይጠቀሳሉ። እነዚህ የምልክት ክፍሎች የአመሰራረት ሂደታቸውን በማየት፣ ምስል በማውጣትና በመማር የሚከሰቱ ናቸው (Danesi 2004:26; Berger 2004:4)።

የትምእርት የውክልና መሰረት የህይወት ተሞክሮ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሊሆን ይችላል። እነዚህን ጉዳዮች መሰረት አድርጎ መመሰል ደግሞ ተግባቦትን ምቹ ያደርጉታል። እንዲሁም አንድ ማኅበረሰብ ስሜቱን፣ ተግባሩንና ባህሪውን በትዕምርቶች አማካይነት ያንጸባርቃል። ትምእርቶች የአንድን ማኅበረሰብ ማንነት፣ እምነት፣ በሰዎች መካከል እና ሰው ከራሱ ጋር ለሚከሰት የተለያዩ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው (Quimby 1976:174)። በተጨማሪም ትምእርቶች የራሳቸው የሆነ ድርብ ፍቺ ያላቸው በመሆኑ የአንድን ማኅበረሰብ አባላት የማግባባትም ሆነ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ፣ ስነልቦና እና መረዳት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ላቅ ያለ ሚና አላቸው።

---

[6]አገልግሎታዊ ምክንያት (Logic of Utility – Functional logic) ቁሶች ወይም ምርቶች ካላቸው የአገልግሎት ፍላጎት አንጻር ይመሰረታሉ። ገበያዊ ምክንያት (Logic of Market – Exchange value) የእሴት ጭማሪ ወይም የአዋጭነት/የአትራፊነት ሁኔታ ታሳቢ ተደርጎ የሚታይ ምልክታዊ ሁኔታ ነው። ከስጦታዊ ምልክት (Logic of gift – Symbolic exchange value) አንጻር ለምሳሌ፤ የእንቁ ቀለበት ስጦታ የፍቅር ምልክት ሆኖ ይቀርባል፤ ቀይ የጽጌረዳ አበባ የፍቅር ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። ሌላው እና የመጨረሻው የክብር ተምሳሌት (Logic of Status – sign value) ተደርጎ የሚታየው ሁኔታ ነው። በዚህም ለምሳሌ አንድ በዋጋ ውድ የሆነ መኪና ያለው ሰው ከሌላቸው አንጻር ሲታይ መኪናው እንደ ክብር ተምሳሌት ተደርጎ ይታያል። በዚህም ቁሱ የመከበሪያ ምልክት ሆኖ ይወሰዳል።

አንድን ትምእርት በመሰረታዊነት ከሦስት ሁነት አኳያ ብያኔ መስጠት ይቻላል። አንደኛው ከኃይማኖት፣ ሁለተኛው የትምእርቱ ተጠቃሚ ከሆነው ማኅበረሰብ ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ ከትምእርቱ ቅርጽና ተግባር አኳያ ነው። በተጨማሪም ትዕምርቱ ከሌላ ትዕምርት ጋር ካለው ዝምድና አንጻር ትርጉም ሊሰጠው ይችላል (Quimby 1976:168)። ከነዚህ መካከል ማኅበራዊ፣ የትምእርቱ ተግባርና ቅርጽ በጥናቱ በዋናነት ብያኔ የተሰጠባቸው ናቸው።

በመጨረሻም በዚህ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ከወስፌ ስፌት ጋር የተያያዙ ትምእታዊ ጉዳዮች አኳያ ትንተና ተደርጓል።

### 2.2.2 የመረጃ መተንተኛ ሞዴል

በጥናቱ የትንተና ክፍል ከሥነልቦናዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ነጥቦች ለመረጃ ማብራሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ነጥቦቹ መነሻ ያደረጉት "የሲግመንድ ፍሮይድ" (Sigmund Freud [1856-1939]) የሰብዕና መዋቅሮች ናቸው። የፍሮይድ የአዕምሮ መዋቅራዊ ሞዴል በሦስት የሰብዕና መዋቅሮች (Structure of Personality) እንደተዋቀረ ምንጮች ይጠቁማሉ (Witting, 2001:213; Guerin, Labor, Morgan, Reesman, & Willingham 2005:158)። እነዚህም ኢድ (id)፣ ኢጎ (ego) እና ልዕለኢጎ (super ego) ናቸው።


**ኢድ፤** ከአዕምሮ ኢንቁ ህሊና ውስጥ የተቀመጠ የሰው ልጅን መሰረታዊ ፍላጎቶች (basic needs)፣ ስሜቶች እና መሻቶች የሚመራ ተፈጥሯዊ ሰብዕና ነው (Witting 2001:213)። ኢድ የሚመራው በ"ትፍስህት መርሆ" (principle of pleasure) በመሆኑ፣ በፍትወት፣ በመፍጠር እና በ"ማውደም" ነፍሳዊ ጉልበት የታመቀ፣ "ፍጹም ራስ ወዳድ"፣ አውድ የማይለይ ህሊናዊ የሆነ፣ አንድን ፍላጎት ለማርካት "ትዕግስት አልባ" የሰብዓና መዋቅር ዓይነት ነው (Witting 2001; Guerin et al. 2005)። በተያያዘም ኢድ ለውስጣዊ ጉዳዮች ቅድሚያ የሚሰጥ፣ በውጫዊ ነገሮች ተጽዕኖ ስር የማይወድቅ፣ ያለገደብ ወይም ያለማዕቀብ የሚሰራ፣ በእርካታ ላይ ብቻ የተመሰረተ፣ አልፎ አልፎ በህልም ዓለም፣ አልያም በአጋጣሚ ሊከሰት የሚችል ሥነሕይወታዊ (biological) የሆነ የሰብዕና መገለጫ ነው።

**ኢጎ፤** ሥነልቦናዊ (psychological) የሆነ፣ ለራስ ቅድሚያ የሚሰጥ፣ ለሚያደርገው ነገር አመክንዮ የሚያቀርብ "ተከላካይ" (defensive) የሚባል የሰብዕና መዋቅር ዓይነት ነው። ይህ ኢድ እና ልዕለኢጎን ለማመጣጠን የሚጥር (moderator)፣ የግላዊነትና የማኅበራዊነት እሳቤዎችን ሚዛናዊ (fair) ለማድረግ የሚተጋ የሰብዕና ዓይነት ነው (Witting 2001; Tyson 2006)። እንዲሁም ኢድ በአያሌ መርሆ እየተመራ የሚፈጥረው የፍላጎት ግፊት ማኅበረሰብ ዘንድ በአመዛኙ ቅቡልነት ሊኖረው ስለማይችል፣ እንዲህ ዓይነቱ ኢውስን ግፊት ሥርዓት እንዲይዝና ከገቢራዊው ዓለም ጋር ስምሙ እንዲሆን በሚያደርስበት ተጽዕኖ የተነሳ "እውነታዊ መርሆ" (principle of reality) እንዲከተል ይገደዳል።

**ልዕለኢጎ፤** ግብረገባዊ እና ማኅበራዊ (Social) የሆነ ሦስተኛው የሰብዕና መዋቅር ዓይነት ነው። ብዙውን ጊዜ በንቁ ህሊና (conscious mind) ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህ ጥሩ መጥፎ ጉዳዮችን (አዎንታዊና አሉታዊ [right and wrong]) መለየት የሚችል፣ ብዙውን ጊዜ ግለሰባዊ በሆኑ ጉዳዮች ሳይሆን፣ "የወል" በሆኑ ማኅበረ ባህላዊ እሳቤዎች ላይ የተመሰረተ ሰብዕና ነው (Witting 2001; Guerin et al. 2005)።

ልዕለኢጎ ለበርካታ የኢድ ገደብ አልባ መሻቶች እና ፍላጎቶች "ገርጋሪ ወይም ገዳቢ" የሰብዕና መዋቅር ነው። ይህ በአንድ ማኅበረሰብ ዘንድ ማኅበረ-ባህላዊ በሆነ አውድ ቅቡልነት የተነፈጋቸው ጉዳዮች በኢንቁ ልቦና (unconscious mind) ገቢራዊ እንዳይሆኑ ይተጋል። በተያያዘም ድርጊቶቹ ከማኅበረሰቡ ማኅበረ-ባህላዊ ጉዳዮች ሳያፈነግጡ መኖር የሚያስችል የአዕምሮ መዋቅር ሞዴል ነው። በዚህም ሰዎች በህይወት ዘመናቸው የሚያደርጓቸውን ቅቡልነት የሌላቸውን ጉዳዮች በሙሉ "ህግ" (limit) የሚያደርግ ቡድናዊ ሰብዕና ነው (Guerin et al. 2005:158)።

ምስል 2. የሰብዕና መዋቅሮች ግንኙነት መግለጫ




ምንጭ፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ስዕላዊ መግለጫ

### 3. የመረጃ ትንተናና ትርጎማ

በዚህ ክፍል ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች የተጠቀሱ ሲሆን፣ እነሱም ከወስፌ ስፌት ጋር የተያያዙ መመሰያዎች የትኞቹ ናቸው? መመሰያዎቹ ምን ጉዳይ ለመግለጽ ዋሉ? የትዕምርት መመሰያ ስልቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ናቸው። በተያያዘም ከትምእርታዊ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ከፍካሬ ልቦና ጋር ግንኙነት ያላቸው የሰብዕና መዋቅሮች ትንተና የተደረገባቸው ናቸው።

#### 3.1 የትምእርት መመሰያ ጉዳዮች

በዚህ ንዑስ ክፍል ስር የተገለጹት መመሰያዎች በተወካይ ስር ሊመደቡ የሚችሉ ሲሆን፣ በእነዚህ አማካይነት ሊገለጽ የተፈለገው ይዘት ደግሞ በወካይ ስር ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው። በወካይ

አማካይነት የሚገለጸው የትርጉም ሂደት ደግሞ እማሬ እና ፍካሬ በሚሉ የፍች ደረጃዎች ሊገለጽ የሚችል ነው (Martin & Ringham 2000:29-42)።

በተያያዘም የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ትምእርቶች በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ (Denesi 2004፡5)። ለአብነት፤ ገሀዳዊና ህሊናዊ በሆነ መልኩ ሊቀርቡ ይችላሉ። እነዚህ መመሰያ ጉዳዮች ከወስፌ ስፌት ስራዎች ጋር በተያያዘ የሚገለጹ ናቸው።

### 3.1.1 ስፌት ተኮር መመሰያዎች

ከወስፌ ስፌት ጋር ግንኙነት ያላቸው መመሰያዎች ከሙያው፣ ከሙያተኛው፣ ከምርት ሂደት፣ ከግብዓት፣ ከማምረቻ መሣሪያ እና ከምርት ጋር ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ በሆነ መልኩ ተያያዥነት አላቸው።

በዚህም ከሙያው ጋር በተገናኘ "ስፌት" ሲገለጽ፣ ከሙያተኛው ጋር ደግሞ "ሰፊ" የሚለው ቃል በአነስታይ ጾታ የተገለጸውን ስያሜ እናገኛለን። ከምርት ሂደት ጋር በተያያዘ የሚገለጸው ጉዳይ በዋናነት ድርጊት ሲሆን፣ በዚህም ቅድመ፣ ጊዜና ድህረ ክንውኖች ይስተዋላሉ። ከማምረቻ መሳሪያዎች ጋር በተያያዘ ሦስት ጉዳዮች በዋናነት ሲጠቀሱ፣ እነዚህም ወስፌ፣ መርፌ፣ ማጭድና መንከሪያ እቃ ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች በተለያዩ ንግግሮች ሲገለጹ ይስተዋላል። ለአብነትም ቀጥሎ የቀረቡትን ማስተዋል ይቻላል።

> እመቤቲቱ ምን ይቼግርሻል ስትባል *ወስፌ* አለች (ንግግር 1)
> ስንደዶና *ወስፌ*፣ ክርና *መርፌ* (ንግግር 39)
> በእናትና ልጅ መካከል፣ *መርፌ* ጠፋ (ንግግር 92)
> አንድ *ማጭድ*፣ ብዙ ስንደዶ ይቆርጣል (46)

ከመስሪያ ግብዓት ጋር በተያያዘ የሚገለጹት ሁለት መልክ አላቸው። እነዚህም መሥፊያና መሰበዣ ናቸው። አክርማ፣ ስንደዶ፣ አለላ፣ ወንጋ እና የተለያዩ የክር ዓይነቶች በመስፊያ ግብዓት ስር ሲመደቡ፣ ሰበዝ፣ ስንበሌጥ፣ የወንጋ ትልታይ እና ጓሳ ደግሞ በመሰበዣ ግብዓትነት የሚመደቡ ናቸው።

ከወስፌ ስፌት ምርት ጋር በተገናኘ የሚጠቀሱት በቁጥር ዘጠኝ ሲደርሱ፣ እነሱም መሶብ፣ ሙዳይ፣ ሌማት፣ አገልግል፣ ድርብ፣ ቁና፣ ቃጤ፣ ሰፌድ እና ወንፊት ናቸው። እነዚህ ምርቶች ካላቸው ቀጥተኛ ፍች ባለፈ ኢቀጥተኛ ያላቸው ሲሆን፣ ይህንንም በቀጣይ የምንመለከተው ጉዳይ ነው።

በዚህ ንዑስ ክፍል ከወስፌ ስፌት ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱ ከሙያ፣ ከሙያተኛ፣ ከምርት ሂደት፣ ከግብዓት፣ ከመስሪያ መሳሪያ እና ከምርት ጋር የተያያዙ የገላጭነት ሚናዎችን ለማየት ተችሏል።

**3.1.1.1 የስፌት ሙያ**

በቀዳሚነት የስፌት ሙያን መሰረት ያደረጉ ገለጻዎች ስንመለከት ሁለት መልክ ይዘው እናገኛለን። ይህም ከይዘት አኳያ የሚገለጸውን የአዎንታዊነት እና የአሉታዊነት ትምእርታዊ ፍች ይመለከታል። በአንድ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚስተዋሉ ትምእርቶች ያላቸው ፍቺ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን እንደሚችል ምንጮች ይጠቁማሉ (Bronner 2007)።

የሙያ ትምእርታዊ እሳቤ ከሙያተኛው ወይም ከአድራጊው ጋር በተያያዘ ሊገለጽ የሚችል ነው። አንድ ሙያ ከሙያተኛው አኳያ በተለያዩ አውዶች ሊገለጽ ይችላል። ሙያን መፈለግ ወይም መማር፣ ሙያተኛ መሆን፣ መጠየቅ እና በሙያ ታዋቂ መሆን በአዎንታ ሲጠቀሱ፣ ከዚህ በተጻጻሪ ያሉት ተግባራትና እሳቤዎች ደግሞ በአሉታ የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው።

አንድ ክንውን ከሙያተኛው ማንነት፣ ሙያው ከሚከወንበት ወቅት አኳያም አዎንታዊና አሉታዊ እሳቤዎች ሊኖሩት ይችላሉ። በዚህ መሰረት አንድን ሙያ መፈለግ ወይም ሙያተኛ መሆን አዎንታዊ እሳቤ ያለው ቢሆንም፣ ከአንድ ማኅበረሰብ ማኅበረ-ባህላዊ ሁኔታ አኳያ ግን የተለየ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ጥናቶች ያስረዳሉ (Silva 2004:21)። በዚህም የስፌት ሙያን ከስርዓተ ጾታ ማንነት አኳያ በማያያዝ ትርጉም የሚሰጥበት ሁኔታ ይስተዋላል።

የስፌት ሙያ ከሚከወንበት ሁኔታና መቼት አኳያ አዎንታዊና አሉታዊ ትምእርታዊ እሳቤዎች ሲኖሩት ይስተዋላል። በዚህም የስፌት ስራን በኃይማታዊ ቀናት እና በዓላት ወቅት መከወን እንደ ክልከላ የሚታይ አሉታዊ ትዕምርት ያለው ተግባር ነው (አብነት ንግግር 9)። በተያያዘም ሙያ የሚቀሰምበትና የሚከወንበት ወቅት የሚጠቅሱ አዎንታዊ ትምእርት ያላቸው ገለጻዎች ያሉ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል ንግግር 3፣ 195 እና 196 ሊጠቀሱ ይችላሉ።

እነዚህ ሥነ ቃላዊ ገለጻዎች ከጊዜ አኳያ ሙያን በልጅነት መልመድ አዎንታዊ ተግባር እንደሆነ፣ ከወራት አኳያ ደግሞ የጥቅምት ወር የስፌት ስራን ለመከወን አመችነት ያለው መሆኑን ንግግሩ መረጃ ሰጪ ሆኖ ቀርቧል። ይህ ሁኔታም ተፈጥሮአዊ የሆነ አመክንዮ ያለው መሆኑን፣ ከአክርማ እና ስንደዶ ቀጨታ መከወኛ ወቅት ጋር አያይዞ መግለጽ ይቻላል። የወስፌ ስፌት ስራ ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ሚና አኳያ ውስንነት ያለበት መሆኑን የሚያመለክቱ አሉታዊ እሳቤ ያላቸው ሥነቃላዊ ገለጻዎችና የቃለ መጠይቅ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

**3.1.1.2 የስፌት ሙያተኛ**

በጥናቱ ወሰን ካለው ማኅበረሰብ ዘንድ ከሚጠቀሱ ሙያተኞች መካከል አንዱ የወስፌ ስፌት ሙያተኛ ነው። ሙያተኝነት አንዱ የሰው ልጅ የማንነት መገለጫ ነው። አንድ ሙያተኛ በሚያከናውነው ክንውን፣ ንግግርና አስተሳሰብ አዎንታዊ እና አሉታዊ ሁኔታዎች ሊስተዋሉበት ይችላሉ።

ሙያተኛው ከሚኖርበት ወይም ከሚሰራበት የአየር ንብረት ሁኔታ አኳያ ትርጉም ያለው ውክልና ይስተዋላል። ለዚህም እንደ ማሳያ ሊቀርብ የሚችለው ንግግር 2 ነው። በዚህ አባባል የሰፊነት ሙያ፣

ሙያተኛው ከሚኖርበት መልክዓ ምድር አኳያ ተወክሎ ቀርቧል። በዚህም የስፌት ሙያተኛ በአመዛኙ በደጋ ስፍራ ሲወከል፣ የሸመና ደግሞ በቆላ ስፍራ ተወክሎ ተገልጿል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከሙያተኛው አንጻር የቀረቡት ገለጻዎች ሁለት ገጽታ ያላቸው ሲሆን፣ እነዚህም አዎንታዊና አሉታዊ ናቸው። በዚህም ከማኅበረሰቡ አስተሳሰብ ጋር የሚሰምሩ ሁኔታዎች በአዎንታ ሲገለጹ፣ ከዚህ በተጻራሪ የቀረቡት ደግሞ አሉታዊ እሳቤ ያላቸው ናቸው። በሌላ አገላለጽ በማኅበረሰቡ ቅቡልነት ያላቸው ንግግሮች እና ድርጊቶች የአዎንታዊነት መመሰያ ሲሆኑ፣ በማኅበረሰቡ እንደ ክልከላ የሚታዩ እና የሚነቀፉት ጉዳዮች ደግሞ የአሉታዊ እሳቤ መመሰያ ሆነው ቀርበዋል።

### 3.1.1.3 የስፌት ግብዓት

የስፌት ግብዓትን መሰረት አድርገው የቀረቡ የተለያዩ ገለጻዎች አቀራረባቸው በአንድ ዓይነት የሥነቃል ቅርጽ አይደለም። ገለጻዎቹ በዋናነት በአባባሎች፣ በፈሊጦችና በቃል ግጥም ቅርጽ የቀረቡ ናቸው። በነዚህ ቅርጾች የተገለጹት የግብዓት ዓይነቶች በቁጥር ስድስት ሲሆኑ፣ እነሱም ስንደዶ፣ አክርማ፣ አለላ፣ ሰበዝ፣ ሰንበሌጥ እና ጓሳ ናቸው።

ግብዓቶቹ ከይዘት አኳያ ያላቸው አወካከል አዎንታዊና አሉታዊ መልክ ያለው ነው። ስንደዶ፣ ሰበዝ እና አለላ በአዎንታ ሲገለጹ፣ ሰንበሌጥና አክርማ ደግሞ በአሉታ ሲገለጹ ይስተዋላል። ምንም እንኳን የገለጻው ፍች ከአውድ አውድ ልዩነት ያለው ቢሆንም። ለዚህም ማሳያ የሚሆኑት በአባሪው ስር የተገለጹት ንግግር 42 እና 43 ይጠቀሳሉ።[7] በነዚህ ንግግሮች መነሻነት እና በሌሎች ቃልግጥሞች ማሳያነት ስንደዶ የጥንካሬ ትምእርት ሆኖ ሲቀርብ፣ አክርማ እና ሰንበሌጥ ደግሞ በአንጻራዊነት በወስፌ ስፌት ስራ ጥንካሬ ያላቸው ተደርገው አይወሰዱም። ለአብነት ቀጥሎ የቀረቡትን ቃልግጥሞች እንመልከት።

...
በተር ታረሳሉ *በስንደዶ* ሞፈር፣
ዓባይ ታረሳሉ በስንደዶ ሞፈር፣
በስንደዶ ሞፈር *ባክርማ* ቀንበር፣
ጅብ ስጋ ተጭኖ ማሰሪያው ጠፍር። (ቃል ግጥም፣ 9)

ሌላው የጥንካሬና የውበት ተምሳሌት ሆነው የቀረቡት ግብዓቶች ሰበዝና አለላ ናቸው። እነዚህ ግብዓቶች ከመስሪያ አኳያ ሰበዝ መሰበኀያ ሲሆን፣ አለላ ደግሞ መስፊያ ነው። በዚህም ይህ የግብዓት ዓይነት አዎንታዊ ትምእርት ያለው ነው።

---

[7] የዝንጀሮ መነኩሴ የሰንበሌጥ አንካሴ (42)፣ የነቂሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ (43)

አለላ በስነ ቃል ቅርጾቹ ዘንድ የውበት መመሰያ ሆኖ ቀርቧል። አለላ ከአጠቃቀም አኳያ ሦስት ዓይነት ሲሆን፣ እነሱም የአክርማ፣ የስንደዶ እና የወንጋ ናቸው። በመስክ ምልከታም ሆነ በቃል ግጥሞቹ ጎልተው የሚስተዋሉት የአክርማ እና የስንደዶ አለላዎች ናቸው። በዚህም እነዚህ የግብዓት ዓይነቶች በተለያዩ የቀለም ዓይነቶች በሚነከሩበት ጊዜ "አለላ" የሚል ስያሜ ያገኛሉ።

የስፌት ግብዓት የሆነው አለላ የውበት መመሰያነቱን የሚያመለክቱ የተለያዩ ቃል ግጥሞች የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ለአብነትም ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት ቃል ግጥሞች ማስተዋል ይቻላል።

> *መሶብ እሰፋለሁ አለላ ባለለ፣*
> የሀገሬ ልጅ ሸጋው ጌታው በምን ይብላ። (ቃል ግጥም 24)
> *ያለላ ሙዳይ፣ ያለላ ሙዳይ፣*
> እቴን በምን አያት ያ ራሳም ድንጋይ። (ቃል ግጥም 30)

በቃል ግጥም 24 የቀረበው አወድ ፍቅር ሲሆን፣ የቃል ግጥሙ ገጸ ሰብ ሴት ናት። በዚህ ቃል ግጥም አለላ አንዱ የመሶብ የመስፊያ ግብዓት እንደሆነና የሚሰፋውም የመሶብ ዓይነት ተራ መሶብ ሳይሆን፣ በተለያዩ የአለላ ዓይነቶች የሚጌጠውን "መሶበ ወርቅ" እንደሆነ ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል። ይህም አፍቃሪዋ ለምታፈቅረው "ጌታዋ" ያላትን የፍቅር ደረጃ ለመስፊያነት ከመረጠችው የግብዓት ዓይነት ጋር በማዛመድ ለመግለጽ የቻለች ይመስላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በቃል ግጥም 30 ላይ የቀረበው ሀሳብ አውዱ ፍቅር ሲሆን፣ ይዘቱ አሉታዊነት ያለው ነው። በመጀመሪያው ስንኝ ላይ የተገለጸው ሀሳብ በለዋጭ ዘይቤ የቀረበ ነው። "እቴን" በሚል የተገለጸው ገጸ ሰብ "ቆንጆ" መሆኗን ለመግለጽ በአለላ ሙዳይ ተወክላ ቀርባለች። እዚህ ላይ ይህ ሀሳብ ሊያጠናክር የሚችል የቃለ መጠይቅ መረጃ ያለ ሲሆን፣ ይህም "የአለላ ሙዳይ ስንል ቆንጆ፣ የሚያምር እንደማት ነው። የአለላ ሙዳይ በሰርግ ጊዜ ለሴት ሙሽራ ትፈለጋለች። ለእናትም ደግሞ ለእጣን፣ ለጭሌ፣ ለሽቶ ማስቀመጫነት ትውላለች" በሚል ተገልጿል።

በቃል ግጥሞች ከተገለጹት አዎንታዊ ትርጉም ካላቸው ግብዓቶች ባለፈ ይህ ሁኔታ በፈሊጦችም ሲገለጽ ይስተዋላል። በዚህም በመመሰያነት የቀረበው ግብዓት ስንደዶ ሲሆን፣ ገለጻውም "ስንደዶ አፍንጫ" (ፈሊጥ 1) ነው። ይህ ገለጻ የአንድ ግለሰብን ውጫዊ ውበት ለመግለጽ የቀረበ ነው። ስንደዶ በተፈጥሮው ቀጥ ያለ ሲሆን፣ የተወላገደ የለውም። በዚህም "እገሌ አበሉ 'ስንደዶ ነው፣ መልካም ስንደዶ ይመስላል፣ አፍንጫው ወለባ ነው' ከተባለ ቀጥ ያለ እና ያማረ ወይም ሸበላ ለማለት የሚገለጽ ነው" የሚለው ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ያስረዳል። በተመሳሳይ ሁኔታ መልኩም ስንደዶ ነው ከተባለ አቋሙ የተስተካከለ መሆኑን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል።

አዎንታዊ መመሰያ ከሆኑት ግብዓቶች ወደ አሉታዊ ወደ ሆኑት ስንመለስ የምናገኘው ሰንበሌጥና አክርማን ነው። አክርማ በቃል ግጥም 9 ላይ ከሰበዝ ጋር በንጽጽር የቀረበ መሆኑ እሙን ነው። የሰንበሌጥ አሉታዊ ፍች መነሻ ልክ እንደ ሰበዝ እና አክርማ ከተፈጥሮአዊ ሁኔታው ጋር የተያያዘ ነው። ይህንን አስመልክተው ከቀረቡት ንግግሮች መካከል "የሰንበሌጥ አንካሴ፣ የዝንጀሮ መነኩሴ" (ንግግር 42) እና "የነቂሎ (የነቶሎ ቶሎ) ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ" (ንግግር 43) የሚሉት ይጠቀሳሉ።

ከዚህ በላይ ለቀረቡት ሁለት ንግግሮች ሰበበ ንጽጽሩ ጥንካሬ አልባነት ነው። በዚህም ሰንበሌጥ በምርት ሂደት ጥቅም ላይ ከዋለ በተግባር እና በገበያ ዘንድ ከሰበዝ አንጻር ውስንነት ያለበት እንደሆነ ለማየት ተችሏል። ግብዓቶች ከመገኛ ስፍራ አኳያ እና ካላቸው ተፈጥሮአዊ ቀለም ወካይ ሆነው ሲቀርቡ ይስተዋላል። ለዚህ አብነት ስንደዶ፣ አከርማና ጓሳ የደጋ አየር ንብረትን ሲገልጹ፣ ሰንበሌጥ ወይና ደጋን፣ እንዲሁም ወንጋ ቆላ አካባቢን ሲወክሉ ይስተዋላል።

የወስፌ ስፌት ግብዓቶች ያላቸውን የመመሰያነት ሚና እና ያላቸውን ፍች ለማየት ተችሏል። ሚናቸው የሃሳብ መግለጫ ሲሆን፣ ያላቸው ፍች ደግሞ አዎንታዊና አሉታዊ ነው። የወስፌ ስፌት ግብዓቶቹ ከመስፊያ እና ከመሰበዣ አኳያ ባላቸው መጠን ሲገለጹ በአዎንታ እና በአሉታ የተገለጹት በተመጣጣኝ ደረጃ ላይ የተገለጹ ናቸው። በተጨማሪም ግብዓቶቹ ከመገኛ ስፍራቸው አኳያ ከአየር ንብረት ሁኔታ እና ካላቸው ተፈጥሮአዊ ቀለም አንጻር የወካይነት ሚና እንዳላቸው በትንተናው ለመገንዘብ ተችሏል።

### 3.1.1.4 የስፌት መሳሪያዎች

የስፌት መስሪያ መሳሪያዎች ካላቸው ቀጥተኛ ፍች ባለፈ ኢቀጥተኛ ፍችም አላቸው። ይህ ደግሞ የማኅበረሰቡን ማኅበረ-ባህላዊ ትርጉም የሚመለከት ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ በተለያዩ የሥነ ቃል ቅርጾች በተደጋጋሚ ሲጠቀሱ የሚስተዋሉት ወስፌ፣ መርፌ እና ማጭድ ናቸው። እነዚህ የሃሳብ መግለጫ ሆነው በዋናነት የቀረቡት በንግግሮች፣ በፈሊጦች እና በቃል ግጥሞች ላይ ነው።

መሥሪያ መሣሪያዎቹ እንደተገለጹበት አውድ አዎንታዊና አሉታዊ ይዘቶች ሲያንጸባርቁ ይስተዋላል። በቀዳሚነት በወስፌ አማካይነት የተገለጸውን ስንመለከት ወስፌ "የሴትነት" እና የሙያተኝነት ትዕምርት ሆኖ ተገልጿል። ለዚህም እንደ ማሳያ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው "እመቤቲቱ ምን ይቼግርሻል ስትባል 'ወስፌ' አለች" (ንግግር 1) የሚለው ንግግር ነው። በጥቅምት 2012 ዓ.ም በተደረገው ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለው እመቤትነት "በመታደል" ሊገኝ ይችላል። ሙያተኝነት ግን ጥረት እና ትጋት ይፈልጋል። ይህም ሁኔታ "ዕድል በመታደል ሙያ በመጋደል" (ንግግር 250) ከሚለው ንግግር ጋር አብሮ የሚሄድ ይመስላል። በዚህም ወስፌ የሙያተኝነት አዎንታዊ መገለጫ ሆኖ ቀርቧል።

ከዚህ በላይ በንግግር ቅርጽ የተገለጸው የወስፌ አዎንታዊ ፍች እንዳለ ሆኖ፣ ወስፌን መሰረት ያደረገ አሉታዊ ፍች እንገኛለን። ይህ ገለጻ የቀረበው በፈሊጥ ሲሆን፣ ድምጸቱ ስድብ ነክ ነው። ገለጻውም ወስፌ "ቂጥ" (ፈሊጥ 12) ሲሆን፣ የአንድ ግለሰብን ውስጣዊና ውጫዊ ማንነት የሚያመለክት ነው። ቀዳሚው ፍች አንድ ስፍራ ተረጋግቶ ወይም አርፎ አለመቀመጥን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ደግሞ ከሰውነት ቅርጻዊ ሁኔታ አኳያ "የቂጣም ተቃራኒ" የሰውነት አካል ያለውን ግለሰብ ለመግለጽ የዋለ ገለጻ ነው።

አዎንታዊና አሉታዊ ሀሳቦች የተንጸባረቁበት ሌላው መሣሪያ ማጭድ ሲሆን፣ ይህም በተመሳሳይ ሁኔታ ለመግለጽ ተችሏል። ማጭድ በስፌት የምርት ሂደት በተለይ በቅድመ የምርት ክንውን

የተለያዩ ግብዓቶችን ከመስክ ለማጨድ እና ለመቁረጥ የሚያገለግል መሳሪያ ነው። በዚህ መልኩ የተገለጸው ማጭድ በተለያዩ ገለጻዎች ውስጥ የተለያዩ ቀጥተኛ ያልሆኑ ፍችዎችን ይዞ ይገኛል።

ከማጭድ ጋር በተያያዘ የቀረቡት ገለጻዎች ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸውን አውዶች መነሻ ያደረጉ ናቸው። የቀረቡት ገለጻዎችም በንግግሮች፣ በፈሊጦች እና በቃል ግጥሞች ነው። በንግግሮች የቀረቡት እና አዎንታዊ ፍች ያላቸውን ገለጻዎች ቀጥሎ የቀረቡትን ማስተዋል ይቻላል።

> አንድ *ማጭድ* ብዙ ስንደዶ ይቆርጣል (ንግግር 46)
> ሰነፍ ሲኮራ *ማጭድ* ይታጠቃል (ንግግር 45)
> አንድ *ማጭድ* ወደቀ (ፈሊጥ 21)

በንግግር 46 የተገለጸው ሃሳብ በአንድ ሥራ ላይ ለስራው አስፈላጊ እና ተገቢ መሳሪያ ሊኖር እንደሚገባ የሚገልጽ ሲሆን፣ በንግግር 45 የተገለጸው ደግሞ ማጭድ የሰራተኝነት፣ የጉብዝና የታታሪነት ትምእርት እንደሆነ በተቃርኖ መልክ የተገለጸበት ነው። እዚህ ላይ ማጭድን አስመልክቶ ተጨማሪ የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። ይህም ማጭድና መዶሻ በተለይም በኤዥያን ሀገሮች በግብርና እና በኢንዱስትሪዎች የሚሰሩ ህዝቦችን እንደሚወክል ይገለጻል። በተያያዘም በቀድሞ ሶቪየት ዩኒየን ዘንድ የኮሚኒዝም ትዕምርት እንደነበርና ይህም በሰንደቃላማቸው ላይ ይጠቀሙበት እንደነበር ምንጮች[8] ይጠቁማሉ (Hornby 2010:676)። በፈሊጥ 21 የቀረበው ገለጻ የዘይቤነት ቅርጽ ያለው ሲሆን፣ አንድ ችግር ወይም ስራ ማለቁን እንዲሁም መቋጨቱን የሚጠቁም ፍች አለው።

ከማጭድ ጋር በተገናኘ አዎንታዊ ይዘቶች እንደቀረቡ ሁሉ በተቃራኒው ደግሞ አሉታዊ ይዘቶችን የሚገልጹ መሰል ገለጻዎች ይስተዋላሉ። ከነዚህም መካከል "ማጭድ እግር" (ፈሊጥ 20) የሚለው ፈሊጣዊ ገለጻ ይጠቀሳል። ይህም የአንድ ሰውን የእግር ሁኔታ በአሉታ ለመግለጽ የገባ ሲሆን፣ ሸፋፋ፣ ከናና የሚል ፍች አለው።

የወስፌ ስፌት መስሪያ መሳሪያዎችን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ገለጻዎች ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ፍች ለመመልከት ተችሏል። ገለጻዎቹ በተለያዩ የሥነ ቃል ቅርጾች የቀረቡ ሲሆን፣ የመስሪያ መሳሪያዎቹ ካላቸው ቀጥተኛ ፍች ባለፈ የማኅበረሰቡን ባህላዊ ፍች ያቀፉ ኢቀጥተኛ ትርጉም እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል።

### 3.1.1.5 የስፌት ምርት ሂደት

ስፌት በማምረት ተግባር ላይ ሦስት ተከታታይነት ያላቸው ደረጃዎች እንዳሉ ተገልጿል [እንዳሉ]። እነዚህም ቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ናቸው። በቅድመ የምርት ሂደት የመቅጨት፣ የመሰንጠቅ፣ የእጅ ትኩሳት እና እጅን አመድ የመቀባት ተግባር በዚህ ደረጃ የሚጠቀሱ ናቸው። ከተግባራቱ መካከል

---

[8] Hammer and Sickle – tools representing the people who work in industry and farming, used on the flag of the former Soviet Union and as symbols of communism (Hornby 2010:676).

"መቅጨት" ከሚለው ገለጻ ውጭ ያሉት በሙሉ አዎንታዊ እሳቤን መሰረት አድርገው የቀረቡ ሲሆን፣ በቀዳሚነት የምናገኘው ገለጻ በቃል ግጥም ቅርጽ የቀረበ ነው።

> …
> ያየና[9] የሚሉት ሀገር ያለማውን ያልማ፣
> አዲሱ ፍቅራችን *ተቀጨ እንደ አክርማ*። (ቃል ግጥም 19)
> …

በስፌት *ሥራ* የመቅጨት ተግባር የዝግጅት ምዕራፍ ነው። ይህ ገለጻ በቅድመ ተግባሩ ካለው ቀጥተኛ ፍች ባለፈ በፍቅር አውድ በቀረበው ቃል ግጥም ኢቀጥተኛ ፍች ይዞ ይገኛል። ገለጻው በዘይቤ መልክ የቀረበ ሲሆን፣ የተፋቃሪዎችን የፍቅር ግንኙነት እክል እንደገጠመው የሚገልጽ ቃል ግጥም ነው።

በቅድመ የምርት ሂደት ላይ እጅን መሰረት አድርገው የቀረቡ ሁለት ድርጊቶች ይስተዋላሉ። እነዚህም የእጅ ትኩሳት እና እጅን አመድ መቀባት ሲሆኑ፣ የስፌት *ሥራው* የተሳካና ሙያተኛ ለመሆን በሚል አዎንታዊ እሳቤ የሚከወኑ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ በጊዜ ማምረት ተግባር ላይ ሦስት ገለጻዎች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህም መወጠን፣ መስፋት እና የወስፌ ስፌት ዙር ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች የስፌት ክፍሎች መሆናቸው አንድ ያደርጋቸዋል። የቀረቡት ገለጻዎች በቃል ግጥም ሲሆን፣ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

> አክርማ *ለመቅጨት* ሲነሱ ሲወድቁ፣
> *መወጠን* ነው እንጂ፣ *መስፋትም* አያውቁ። (ቃል ግጥም 11)
> ሰው በድየ ነበር እኔም እንደዋዛ፣
> ቁናው ቁናየ ነው፣ *የእኔ ዙሩ በዛ*። (ቃል ግጥም 3)

ቃል ግጥም 11 በቅኔ ቅርጽ የቀረበ ሲሆን፣ ህብረ ቃሉ መስፋት የሚለው ቃል ነው። ሰሙ ወይም ቀጥተኛው ፍች የወስፌ ስፌትን ከመወጠን በስተቀር የመስፋት ችሎታ የላቸውም የሚል ፍች አለው። ወርቁ ወይም ኢቀጥተኛ ፍቹ በጅምር መቅረት እንጂ፣ ዘለቄታ የላቸውም የሚል ፍች አለው። በዚህ መነሻነት መወጠን የመጀመር ገላጭ ሲሆን፣ መስፋት ደግሞ የችሎታ እና የጨራሽነት ወካይ ሆኖ የቀረበ አዎንታዊ ፍች ነው። በዚህም ተወጠነ የሚባለው ቁጥሩ እንዳለ ሆኖ የመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ቀጭን ዙሮች ተደምረው ነው።

[9] ይህ አገላለጽ የሥፍራ መጠሪያን ለማመልከት የገባ ነው።




ፎቶግራፍ፤ የወስፌ ስፌት መወጠኛ ክፍል

ቃል ግጥም 3 የስፌት ክፍል የሆነውን ዙር መሰረት አድርጎ የቀረበ ነው። በዚህ ግጥም አውድ "ዙር" የወከለው ቀጥተኛ ፍች የስፌት አካልነትን ነው። ቀጥተኛ ያልሆነው ደግሞ መጠንን እና መለኪያ በመሆን የገላጭነት ሚና እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።

ከድህረ የምርት ሂደት ተግባራት ከሚጠቀሱ ገለጻዎች መካከል መለጎም[10] አንዱ ነው። አንድ የወስፌ ስፌት ምርት ከዚህ አኳያ የተለጎመና ያልተለጎመ በሚል ይመደባል። የመለጎም ተግባር የስፌት ምርቱ ያለ ጊዜው ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን በሚል እሳቤ የሚከወን ሲሆን፣ በተቃራኒው ደግሞ አለመለጎም በአሉታ የሚታይ ድርጊት ነው። ለዚህም ይመስላል አንድ ያልተለጎመ የስፌት ምርት "ስድ" በሚል ሲገለጽ የሚስተዋለው።

የስፌት የምርት ሂደትን መሰረት ያደረጉ ገለጻዎችን እና ድርጊቶችን ያላቸውን የገላጭነት ፍችና ሚና ለማየት ተችሏል። የቀረቡት ድርጊቶችና ገለጻዎች ካላቸው የፍች ደረጃ አኳያ ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ አወካከል አላቸው። በተያያዘም መመሰያዎቹ ካላቸው ይዘት አኳያ አዎንታዊ እና አሉታዊ ፍች እንዳላቸው በትንተናው ለመመልከት ተችሏል።

### 3.1.1.6 የስፌት ምርቶች

ከዚህ በፊት በተገለጸው መሰረት የስፌት ምርቶች ካላቸው ቀጥተኛ ፍች ባለፈ ቀጥተኛ ያልሆነ ምንነት እንዳላቸው በጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህ ምርቶች በማኅበረሰቡ ዘንድ ከሚሰጣቸው ደረጃ እና አመለካከት ባለፈ በተለያዩ የሥነ ቃል ቅርጾች ሲገለጹ ይስተዋላል። እንዲህ ዓይነቱ ገለጻ በዋናነት ጎልቶ የሚስተዋለው በንግግሮች፣ በፈሊጦችና በቃል ግጥሞች ላይ ነው።

---

[10] መለጎም አንድ የወስፌ ስፌት ምርት ማለትም መሶብ፣ ሰፌድ፣ ቁና፣ ድርብ፣ አገልግልና ወንፊት በቆዳ፣ በስንደዶ ፈትል እና በፕላስቲክ ውጤቶች የመለበድ እና የመሸፈን ተግባር ነው።

ከሥነቃላዊ ጉዳዮች ትንተና መነሻነት ለመረዳት እንደተቻለው በቁጥር አስር የሚደርሱ የወስፌ ስፌት ምርቶች ተገልጸው ተስተውሏል። እነዚህም መሶብ፣ ሌማት፣ ሙዳይ፣ አገልግል፣ ሰፌድ፣ ቁና፣ ድርብ፣ ቃጤ፣ ወንፊት እና የመሶብ አንዱ ዓይነት የሆነው መሰበ ወርቅ ናቸው። ከነዚህ መካከል ቁና እና ወንፊት በሥነ ቃል ቅርጾቹ ተደጋግመው ተገልጸዋል። እነዚህ የስፌት ምርቶች የተገለጹበት ሁኔታ ሦስት መልክ ያለው ነው። እነዚህም ከስፌት ምርቶቹ ተፈጥሮ፣ ተግባር እና ጥቅም ላይ ከሚውሉበት አውድ ጋር የተያያዘ ነው። የአገላለጽ ሁኔታው አዎንታዊና አሉታዊ እሳቤን መሰረት ያደረገ ነው።

የስፌት ምርት የሆነው ቁና ካለው ቀጥተኛ ፍቺ ባለፈ ባህላዊ ፍች ይዞ ይገኛል። ይህም በዋናነት ከስፌት ምርቱ ተግባር ጋር ተዛምዶ የተገለጸ ሲሆን፣ ለዚህም ቀጥሎ የቀረቡትን ቃል ግጥሞች ማስተዋል ይቻላል።

ሰው በድየ ነበር እኔም እንደ ዋዛ፣
*ቁናው ቁናየ* ነው ትንሽ ዙሩ በዛ። (ቃል ግጥም 3)
አፈር አታብዙባት ይበቃታል *ቁና*፣
እሷ በልጆቿ አትጨክንማና። (ቃል ግጥም 16)

በቃል ግጥም 3 ላይ የተገለጸው ይዘት በደል ሲሆን፣ በቁና መልክ የተገለጸው ደግሞ የበደሉን መጠንና ደረጃ የሚመለከት ነው። እንዲሁም ሰው በድየ ነበር በኔ ላይ ብድሩ ደረሰብኝ የሚል ፍች እንዳለው የቃለ መጠይቅ መረጃ ያመለክታል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በቃል ግጥም 16 ላይ የተገለጸው ጉዳይ ከቁና ቀጥተኛ ተግባር ጋር ግንኙነት ያለው ነው። ቁና ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል ቀዳሚው የመለኪያነት ተግባር ነው። በዚህም ከሞት አውድ አኳያ "ይበቃታል ቁና" ሲል አነስተኛ የአፈር መጠን የሚያመለክት ገለጻ ነው።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የቃል ግጥም ገለጻዎች ባለፈ በተለያዩ ፈሊጦች ቁናን መነሻ ያደረጉ ገለጻዎች ይስተዋላሉ። እነዚህ ገለጻዎች አዎንታዊና አሉታዊ ይዘት ያላቸው ሲሆን፣ የሚከተሉትን አብነቶች እንመልከት።

የወንዶች ቁና (ፈሊጥ 13)
ዓይን በቁና ይሰፍራል (ፈሊጥ 11)
መሬት ቁና ሆነች (ፈሊጥ 10)

የወንዶች ቁና የሚለው ገለጻ በአንድ ማኅበረሰብ ዘንድ ጀግና፣ ደፋር እና የወንድነት መለኪያ ለሆነ ግለሰብ የሚቀርብ ገለጻ ነው። በፈሊጥ 11 እና 10 የተገለጸው ሃሳብ አዎንታዊነት የሌለው ነው። "ዓይን በቁና ይሰፍራል" የሚለው ገለጻ የአንድን ግለሰብ የክፍት ደረጃ ለመግለጽ የዋለ ነው። በተመሳሳይ "መሬት ቁና ሆነች" የሚለውም የጭንቀትን ደረጃ እና ሁኔታ ለመግለጽ የቀረበ ነው። ይህን ገለጻ አቶ ሰይድ አደም እና ዘውዴ ደሳለኝ የተባሉት መረጃ አቀባዮች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተከሰተው ጦርነት (2013 እስከ 2014 ዓ.ም) ምክንያት በጦርነት ስር ከነበሩት ከተሞች

መካከል ኮምቦልቻ አንዷ ነበረች። በዚህም ምክንያት ያን የጦርነት ወቅት "ምድር ቁና ሆነች፣ ምድር ቃጤ ሆነች የሚባለው እኮ ይህ ወቅት ነው" በማለት አጫውተውኛል።

በሁለት ሰዎች መካከል ያለን ልብ ለልብ የመተዋወቅ ደረጃን ለመግለጽ "የአብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፍራል" (ንግግር 47)፣ አለከለከ ወይም ደነገጠ ለማለት ቁና ቁና ተነፈሰ (ፈሊጥ 14) የሚሉ ገለጻዎችን እናገኛለን። እስካሁን የተመለከትነው ቁናን መሰረት ያደረጉ ገለጻዎች ነው። በመቀጠል ወንፊትን መሰረት ያደረጉ መሰል ገለጻዎች እንደሚከተለው እናያለን። በቅድሚያ ማሳያዎችን እንመልከት።

> ጊዜ ወንፊት ነው ሁሉን ያጠራል (ንግግር 32)
> ከሰው ፊት ውሃ በወንፊት (ንግግር 36)
> የፍጅት ወራት እሳት በወንፊት (ንግግር 37)

እነዚህ ሦስት ንግግሮች የጋራ ጉዳይ ያላቸው ይመስላል። ይህም ንግግሮቹ ከወንፊት ተፈጥሮና ተግባር ጋር በተገናኘ መልኩ የተገለጹ ናቸው። በንግግሮቹ የሰው ልጅ፣ ጊዜ እና ወራት በወንፊት ተወክለው ተገልጸዋል። የገለጻው ይዘት አዎንታ እና አሉታን መነሻ ያደረገ ነው። የሰው ፊት እሳት ነው፤ እንደሚባለው ሁሉ የሰውን ፊት ማየት ያለውን አስከፊነት ለመግለጽ፣ ሊሆን የማይችለውን ውሃን በወንፊት ማድረግ ይሻላል የሚል አንድምታ ያለው ገለጻ በንግግር 36 የቀረቡት አንጻራዊ ፍች ያላቸው ሐረጎች ማሳያ ናቸው።

በጥናቱ ለማሳያነት በሚል ቁና እና ወንፊት መሰረት ያደረጉ ገለጻዎችና ትንተናዎች የቀረቡ ቢሆንም፣ ሌሎች የወስፌ ስፌት ምርቶችን መነሻ አድርገው የቀረቡ አሉ። ለአብነት ሙዳይ፣ መሶብ እና ሰፌድ ከሴት ልጅ ባህሪ እና ከእናትነት ጋር በተገናኘ ቀርበዋል። ድርብ ወይም እንቅብ ከመጠን አኳያ ከትልቅነት፣ ቃጤ ደግሞ በተቃራኒው ከትንሽነት ጋር በተገናኘ ተገልጸዋል።

የወስፌ ስፌት ምርቶች መሰረት ያደረጉ ገለጻዎች ካላቸው ቀጥተኛ ፍች ባሻገር ያለውን ትምእርት ለማየት ተችሏል። እነዚህ ገለጻዎች ከስፌት ምርቶቹ ቀጥተኛ ተግባር፣ ቅርጻዊ እና ተግባር ላይ ከሚውሉበት አውድ አኳያ የተገለጹ ናቸው። የገለጻዎቹ ይዘትም አዎንታዊ እና አሉታዊ በሆነ ፈርጅ የተገለጹ ናቸው።

### 3.2 የትምእርት መመሰያ ስልቶች

በዚህ ስር የሚጠቀሱት ጉዳዮች የመመሰያዎቹ መነሻ ምንድን ነው? የሚለውን የሚመለከት ሲሆን፣ ይህም በከለሳ ድርሳናት በሥነትምእርት ስር ለመግለጽ እንደተፈለገው ምስስሎሻዊ፣ ምክንያታዊ እና ስምምነታዊ የሚሉትን የሚመለከት ነው። እነዚህ የትዕምርት መመሰያዎች ከሙያ፣ ሙያተኛ፣ ግብዓት፣ መሥሪያ መሣሪያ፣ የምርት ሂደት እና ምርቶች ጋር በተገናኘ የቀረቡ ናቸው።

### 3.2.1 ምስስሎሻዊ ስልት

ምስስሎሻዊ ስልት በዋናነት ከሦስት ነገሮች ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ እነዚህም ቅርጻዊ፣ ድርጊታዊና ይዘታዊ ናቸው። ከነዚህ መካከል ቅርጻዊ ምስስሎሽ ከሌሎቹ በአንጻራዊነት ጎልቶ የሚስተዋል ነው።

ከወስፌ ስፌት ጋር ግንኙነት ያላቸው ምስስሎሽ ከግብዓት፣ ከመስሪያ መሳሪያ፣ ከምርት ሂደት፣ ከስፌት ቅርጻዊ ክፍሎች እና ከምርቶች ጋር ጎልተው የሚታዩ ናቸው። በግብዓት ረገድ ስንደዶ፣ ሰበዝ፣ አለለ፣ ሰንበሌጥ እና ጓሳ ይጠቀሳሉ። ስንደዶ እና ሰበዝ ካላቸው ተፈጥሯዊ ጥንካሬ፣ እንዲሁም ውበት ጋር በተያያዘ ተገልጸዋል። አለላ ካለው ቅርጻዊ መልክ አኳያ በውበት ተመስሎ ቀርቧል። ሰንበሌጥ ካለው ተፈጥሯዊ እና ቅርጻዊ ሁኔታው አንጻር የሰበዝና የስንደዶ ተቃራኒ ሆኗ ተገልጿል።

በመሥሪያ መሣሪያ ረገድ ወስፌ፣ ወለባ፣ መርፌ እና ማጭድ ከስፌት አኳያ ይጠቀሳሉ። በነዚህ መሳሪያዎች ተመስለው የቀረቡት ጉዳዮች ከቅርጻዊና ከተፈጥሯዊ ሁኔታቸው ጋር በተያያዘ የተገለጹ ናቸው። ማጭድ ካለው ቅርጻዊ ሁኔታ አንጻር “ማጭድ እግር...” (ፈሊጥ 20) በሚል ሲገለጽ ይስተዋላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ወስፌ ካለው ቅርጻዊ መነሻነት በፈሊጥ ሲገለጽ ይስተዋላል። በዚህም “ወስፌ ቂጥ...” (ፈሊጥ 12) የሚለው ገለጻ የሚጠቀስ ሲሆን፣ ይህም ወስፌ በገቢር “በቂጡ” በኩል ማስቀመጥ ቢፈለግ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ስሪቱ ይህን ሁኔታ አይፈቅድለትም።

ስንደዶ እና ወለባ[11] በተፈጥሮአቸው ቀጥ ያሉ ከመሆናቸው ጋር በተገናኘ “ወለባ አፍንጫ...” (ፈሊጥ 1) በሚል ገለጻ የሰው አፍንጫ የተስተካከለ እና ውበት ያለው መሆኑን ለመግለጽ የሚውሉ አጠቃቀሞች ናቸው። ይህም የነዚህን ቅርጻዊ ሁኔታ ከሰውነት ውጫዊ መልክ ጋር በምስስሎሽ የቀረበ ስነ ቃላዊ ገለጻ ነው።

“ክርና መርፌ ሆነውዋል” (ፈሊጥ 26) የሚለው ገለጻ በሴትና በወንድ መካከል ያለውን ጾታዊ ሩካቤ ለመግለጽ የዋለ ነው። በዚህ ገለጻ ክር በወንድ ሲወከል፣ መርፌ ደግሞ በሴት ተወክሎ ቀርቧል። የአወካከሉ ሁኔታ ቅርጻዊ ምስስሎሽን መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ ረገድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የወንድ ብልት በዱላ፣ በዛፍ፣ በዥንጥላ፣ በቢለዋ፣ በእርሳስ፣ በመዶሻ ትምእርቶች ሲወከል፣ የሴት ብልት ደግሞ፣ በዋሻ፣ በጠርሙስ፣ በሳጥን፣ በበራፍ፣ በአበባ ትምእርቶች እንደሚመሰል ተገልጿል (Dorson 1963:105)። ይህ ገለጻ የወስፌ ስፌት መሥሪያ መሣሪያዎች እና ግብዓቶች ከቀደምት ጥናቶች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትምእርታዊ ግኝት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።

በምርት ሂደት ውስጥ የወስፌ ስፌት ቅርጻዊ ሁኔታዎች እና የአሰራር ስልቶች ይጠቀሳሉ። የስፌት ቅርጻዊ ሁኔታዎች ከተፈጥሯዊ እና ሰዋዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ናቸው። ሜዳና ዳገት የሚባሉት የስፌት ክፍሎች መጠሪያ ሆነው ጥቅም ላይ ውለዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንገት፣ ጥርስ፣ እግር እና እናት የሚሉት ከሰው ልጅ ጋር በተያያዘ የቀረቡ ምስስሎሻዊ መጠሪያዎች ናቸው።

---

[11] ጸጉር ላይ የሚሰካ ከብር ወይም ከወርቅ የሚሰራ የጌጥ ዓይነት፤ እንዲሁም ከኛርት ላባ የሚገኘው “ጃርት ወለባ” በሚል ይታወቃል።

በወስፌ ስፌት የምርት ሂደት የአሰራር ዘዴዎች የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ከአሰራር ብልሃት አኳያ ሦስት ጉዳዮች በዋናነት ይጠቀሳሉ። እነዚህም ፀሐይ ግባት፣ አልባሶና የመስቀል ቅርጽ ናቸው። እነዚህ የአሰራር ዘዴዎች ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ መነሻ አላቸው። ፀሐይ ግባት አንዱ ተፈጥሯዊ መነሻ ሲሆን፣ ከፀሐይ መግባት ጋር በተያያዘ ተመስሎ የቀረበ ምስያ ነው። አልባሶ አንዱ የጸጉር አሰራር ዓይነት ነው። ይህም ዘዴ በስፌት የምርት ሂደት ላይ በመስስሎሽ ጥቅም ላይ ይውላል። በተለይ በመሶብ፣ ሙዳይ እና ቃጫ የስፌት ዓይነቶች ላይ በአመዛኙ ጥቅም ላይ ይውላል። ጉንጉን የአሰራር ዓይነትም ከገብስ ዛላ ተፈጥሮአዊ ቅርጽ አኳያ ምስስሎሽ ይስተዋልበታል። በተያያዘ በስፌት ምርቶች ላይ የሚውለው የመስቀል ቅርጽ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሰው ሰራሽ ምስስሎሽ ጋር በተገናኘ የሚጠቀስ ነው።

ከስፌት ምርቶች ጋር በተያያዘ የሚገለጸው መመሳሰል ሁለት መልክ ያለው ሲሆን፣ ይህም ከቅርጻዊና ድርጊታዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የሚታይ ነው። በዚህ ረገድ ቤዶ (እንቅብ)፣ ሰፌድ እና ወንፊት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። ከቤዶ የቅርጽ ሁኔታ ጋር በተያያዘ “ቤዶ አፍ…” (ፈሊጥ 3) የሚል ፈሊጣዊ ገለጻ እናገኛለን። የእባብን ቅርጻዊ ሁኔታ ለመግለጽ “የመስከ ሰፌድ…” (ፈሊጥ 6) የሚል ፈሊጣዊ ገለጻ እናገኛለን። ይህም እባብ ተጠቅሎ የሚገኝበትን ቅርጻዊ መልክ የሚያሳይ ነው። ይህም የሰፌድ የአሰራር ቅርጽ መሰል መነሻ ያለው ይመስላል። በተመሳሳይ ሁኔታ “የሸረሪት ሌማት…” (ቃል ግጥም 29) የሚለው ገለጻ ከሌማት ቅርጻዊ ሁኔታ ጋር በተገናኘ የቀረበ ነው። የወንፊት ተግባር ከሰው ልጅ ግብር ጋር ተመስሎ ቀርቧል።

### 3.2.2 አመክንዮታዊ ስልት

በዚህ ስር የተጠቀሱት ስልቶች መነሻቸው ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ሊሆኑ ይችላሉ። መሰረታዊ መገለጫቸው ገቢራዊነት እና እውነታ ላይ መመስረት ነው። በዚህም ትምእርቱ የሚኖረው እሳቤ ከነዚህ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ነው።

ከምክንያታዊነት ስልት አንጻር በዋናነት በወስፌ ስፌት የሚጠቀሱት ግብዓቶችና መስሪያ መሳሪያዎች ናቸው። ግብዓቶቹ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተፈጥሮአዊ መካከል የተክል ዓይነቶች፣ ማዕድናት እና የአየር ንብረት ሁኔታዎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ከመሥሪያ እና ግብዓት መካከል ስንደዶ፣ ሰበዝ፣ ወይራ፣ ወርሳቢሳ እና ግራዋ ተፈላጊ እና ተመራጭ መሆናቸው፣ እንዲሁም አዎንታዊ እሳቤ መያዛቸው ከተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው የመነጨ ምክንያታዊ መነሻ ነው። የፀሐይ የድርቀት እና የመቀት መነሻ መሆን፣ እንዲሁም የውሃ የእርጥብነት መነሻ ከተፈጥሮአዊ ባህሪ ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱ ምክንያታዊነት ነው። የብረት የጠንካራነት እሳቤ መያዝ፣ የአመድ በምረት ሂደት ጥቅም ላይ መዋል፣ ከማዕድናቱ ተፈጥሮአዊ ስሪት ጋር የተያያዘ ነው። ግብዓቶች በሚገኙበት የአየር ንብረት ሁኔታ አኳያ መገለጻቸው እና ትምእርት መሆናቸው ተፈጥሮአዊ መነሻ ያለው ነው። ከግብዓት አኳያ የመሥፊያ ግብዓቶች እና የክሮች ተመራጭነት ግብዓቶቹ ካላቸው የተለማጭነት ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ጋር ግንኙነት ያለው ነው።

### 3.2.3 ስምምነታዊ ስልት

በዚህ ስልት የሚነሱት ጉዳዮች በዋናነት በማኅበረሰቡ ዘንድ ከማኅበረ ባህላዊ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች በአጠቃላይ አዎንታዊና አሉታዊ እሳቤ አላቸው። ስልቱ በሙያና ሙያተኛ፣ በግብዓት፣ በመስሪያ መሳሪያ፣ በምርት ሂደት እና በምርቶች ይገለጻል።

የስራ ክፍፍል በዋናነት ከማኅበረ ባህላዊ ጋር ግንኙነት ያለው እና በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ ልዩነት ያለው መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ (Silva 2004:21)። በዚህም ከወስፌ ስፌት ምርቶች በተያያዘ መሶብ፣ ሙዳይ እና ወንፊት ከሴትነት እና ከእናትነት ጋር በተያያዘ ተገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ እንዲሁም አዎንታዊና አሉታዊ በሚል ፍቻዊ ምድብ ሊገለጹ የሚችሉ ናቸው።

## 3.3 ስፌት ተኮር የፍካሬ ልቦና ጉዳዮች

ከዚህ በፊት በጥናቱ የአጠናን ዘዴ ክፍል የመረጃ ማብራሪያ ሞዴል ስር የፍሮይድ የሰብዕና መዋቅሮችን ለመግለጽ ተሞክሯል። በዚህ መነሻነት ከኢድ፣ ኢጎ እና ልዕለኢጎ ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች ለመተንተን ተሞክሯል።

በኢድ የሰብዕና መዋቅር ግላዊነት ያላቸው አስተሳሰቦች፣ ፈጠራዊ ጉዳዮች፣ ግላዊ መሻቶች፣ ህልሞች፣ ሩካቤያዊ እሳቤዎች፣ እንደግል ጥሩና መጥፎ ሊባሉ የሚችሉ ንግግሮችና ድርጊቶች በዚህ ሰብዕና ስር ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው። በምርቶች ላይ የሚቀርቡ ንቅሳቶች (ዲዛይኖች) እና ፈርጦች በኪናዊነት ስር ሊጠቀሱ የሚችሉ ትምእርታዊ እሳቤዎች ናቸው።

ሁለተኛው የሰብዕና መዋቅር ኢጎ ሲሆን፣ በዚህ መዋቅር የተለያዩ መንስኤዎች እና ሚዛናዊ የሆኑ ነጥቦች ይጠቀሳሉ። በግላዊና በማኅበራዊ ጉዳዮች መካከል የሚስተዋሉ ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች ሚዛን እንዲጠብቁ የሚደረጉት በኢጎ የሰብዕና መዋቅር ነው። ለዚህ ማሳያም በሥነ ቃላዊ ጉዳዮች ዘንድ በክልከላ ንግግሮች የሚጠቀሱት ምክንያቶች፣ ሥነልቦናዊ እና ሚዛናዊ እሳቤዎች በዚህ አግባብ የሚታዩ ናቸው።

በመጨረሻም የሚጠቀሰው የሰብዕና መዋቅር ልዕለኢጎ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። በዚህም በማኅበረሰቡ ቅቡልነት ያላቸው እሳቤዎችና ድርጊቶች ይጠቀሳሉ። በማኅበረሰብ ደረጃ የሚስተዋሉ ማኅበረ ባህላዊ ክንውኖች፣ ደንቦች፣ ስምምነቶች እና ክልከላዎች በዚህ አግባብ በማሳያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በዚህ የሰብዕና መዋቅር አንድ ጉዳይ ጥሩ ወይም መጥፎ ሊባል የሚችለው ከወል እይታ አኳያ ነው። በአንጻሩ ግላዊ ጉዳዮች በአመዛኙ ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም።

በግልም ሆነ በማኅበረሰብ ደረጃ ሊከሰቱ ለሚችሉ ሰብዕናዊ መዋቅሮች ሦስት መንስኤዎች ይጠቀሳሉ። እነዚህም አካባቢያዊ፣ ውልደታዊ እና የሁለቱ ቅንጅቶች ናቸው። ከአካባቢያዊ መንስኤዎች አኳያ በሙያዎቹ የሚስተዋሉ የሥራ ክፍፍሎች፣ የግብዓት አጠቃቀም፣ የምርት

አጠቃቀም፣ የሙያተኛ ምንነት እና ሌሎች ጉዳዮች የሚጠቀሱ ናቸው። በግብዓት ስንደዶና አክርማ የደጋ አካባቢ ግብዓቶች መሆን፣ የወንጋ ግብዓቶች የቆላ አካባቢ ግብዓት ማሳያነት ይጠቀሳሉ።

ከውልደትና ተፈጥሮአዊ ከሆኑ ጉዳዮች አኳያ ደግሞ በሙያዎቹ ወንድነት ከጥንካሬ ጋር በተያያዘ ሲገለጽ ሴትነት ደግሞ ከውበታዊ እና ከትዕግስታዊ ጋር በተገናኘ ተገልጸዋል። ከአካባቢያዊና ከውልደታዊ ጉዳዮች አኳያ በማኅበረሰቡ የሚስተዋሉት የአመጋገብ ሁኔታ፣ አውድ፣ የእጅ ትኩሳት፣ እጅን ዓመድ መቀባት፣ የእውቀትና የልምድ ሁኔታዎች እና ከሙያዎቹ ጋር የተያያዙ የክልከላ ድርጊቶች በዚህ ረገድ የሚጠቀሱ ሰብናዊ መንስኤዎች ናቸው።

በዚህ ክፍል ከሰብዕና መዋቅሮች እና ከመንስኤዎች ጋር በተያያዙ ገለጻ ለማድረግ ተችሏል። እነዚህ ጉዳዮች ከግላዊና ማኅበረሰባዊ እሳቤዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ሰብዕናዊ መዋቅሮቹ በአመዛኙ በአዎንታዊ እና በአሉታዊ የፍች ደረጃዎች ሊገለጹ የሚችሉ ናቸው።

## 4. ማጠቃለያ፣ ድምዳሜና ምክረሃሳብ

ስፌት ተኮር ትምእርታዊ ጉዳዮችን መተንተን የዚህ ጥናት ዓላማ ነው። በዚህ ጥናት ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ቀርበዋል። እነዚህም ከወስፌ ስፌት ጋር የተያያዙ ትምእርታዊ መመሰያዎች እና የፍካሬ ልቦና ጉዳዮች ናቸው። ከትምእርታዊ መመሰያ ጉዳዮች ጋር ስፌት ተኮር መመሰያዎች እና የትምእርት መመሰያ ስልቶች ይጠቀሳሉ።

ከወስፌ ስፌት መመሰያዎች ጋር በተገናኘ ከሙያው፣ ከሙያተኛው፣ ከምርት ሂደት፣ ከግብዓት፣ ከማምረቻ መሣሪያ እና ከምርት ጋር ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ በሆነ መልኩ ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች የታዩበት ነው። በዚህም ከሙያው ጋር በተገናኘ ስፌት ሲገለጽ፣ ከሙያተኛው ጋር ደግሞ ሰፊ የሚለው ስያሜ እናገኛለን። ከምርት ሂደት ጋር በተያያዘ የሚገለጸው ጉዳይ በዋናነት ድርጊት ሲሆን፣ በዚህም ቅድመ፣ ጊዜና ድህረ ክንውኖችን እናገኛለን። ከማምረቻ መሣሪያዎች አንጻር ሦስት ጉዳዮች በዋናነት ሲጠቀሱ እነዚህም ወስፌ፣ መርፌ፣ ማጭድና መንከሪያ እቃ ናቸው።

ከመስሪያ ግብዓት አኳያ የሚገለጹት ሁለት መልክ አላቸው። እነዚህም መስፊያና መሰበዣ ናቸው። አክርማ፣ ስንደዶ፣ አለላ፣ ወንጋ እና የተለያዩ የክር ዓይነቶች በመስፊያ ግብዓት ስር ሲመደቡ፣ ሰበዝ፣ ሰንበሌጥ፣ የወንጋ ትልታይ እና ጓሳ ደግሞ በመሰበዣ ግብዓት የሚመደቡ ናቸው። እንዲሁም በወስፌ ስፌት ምርት ስር የሚጠቀሱት መሶብ፣ ሙዳይ፣ ሌማት፣ አገልግል፣ ድርብ፣ ቁና፣ ቃጨ፣ ሰፌድ እና ወንፊት ናቸው።

በወስፌ ስፌት የሚስተዋሉት መመሰያዎች የራሳቸው የሆነ ኢቀጥተኛ ፍች አላቸው። ይህ ፍች ከይዘት አኳያ በአዎንታዊና በአሉታዊ ሊመደብ ይችላል። በዚህም በማኅበረሰቡ ቅቡልነት ያላቸው ንግግሮች እና ድርጊቶች የአዎንታዊነት ሲሆኑ፣ በማኅበረሰቡ እንደ ክልከላ የሚታዩ እና የሚነቀፉት ጉዳዮች ደግሞ የአሉታዊ እሳቤ ሆነው ቀርበዋል። ለአብነት አዎንታዊ ከሆኑት ግብዓቶች መካከል ሰብዝ እና ስንደዶ ሲጠቀሱ፣ ሰንበሌጥና አክርማ ደግሞ በአንጻራዊነት በአሉታ የተገለጹ ናቸው።

የትምእርት መመሰያ ስልቶች ሦስት ሲሆኑ፣ እነዚህም ምስስሎሻዊ፣ አመክንዮታዊ እና ስምምነታዊ ናቸው። ከስፌት ጋር ግንኙነት ያላቸው ምስስሎሽ ከግብዓት፣ ከመሥሪያ መሣሪያ፣ ከምርት ሂደት፣ ከስፌት ቅርጻዊ ክፍሎች እና ከምርቶች ጋር ጎልተው የሚታዩ ናቸው። በግብዓት ረገድ ስንደዶ፣ ሰበዝ፣ አለለ፣ ሰንበሌጥ እና ጓሳ ይጠቀሳሉ። ስንደዶ እና ሰበዝ ካላቸው ተፈጥሮአዊ ጥንካሬ፣ እንዲሁም ውበት ጋር በተያያዘ ተገልጸዋል። አለላ ካለው ቅርጻዊ መልክ አኳያ በውበት ተመስሎ ቀርቧል። ሰንበሌጥ ካለው ተፈጥሮአዊ እና ቅርጻዊ ሁኔታው አንጻር የሰበዝና የስንደዶ ተቃራኒ ሆኗ ተገልጿል። በመሥሪያ መሣሪያ ረገድ ወስፌ፣ ወለባ፣ መርፌ እና ማጭድ ከስፌት አኳያ ይጠቀሳሉ። በነዚህ መሳሪያዎች ተመስለው የቀረቡት ጉዳዮች ከቅርጻዊና ከተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ጋር በተያያዘ የተገለጹ ናቸው።

በስፌት የምርት ሂደት የአሰራር ዘዴዎች የሚጠቀሱ ሲሆን፣ እነዚህም ፀሐይ ግባት፣ አልባሶና የመስቀል ቅርጽ ናቸው። እነዚህ የአሰራር ዘዴዎች ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ መነሻ አላቸው። ፀሐይ ግባት አንዱ ተፈጥሮአዊ መነሻ ሲሆን፣ ከፀሐይ መግባት ጋር በተያያዘ ተመስሎ የቀረበ ምስያ ነው። አልባሶ አንዱ የጸጉር አሰራር ዓይነት ነው። ይህም ዘዴ በስፌት የምርት ሂደት ላይ በመስስሎሽ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ዘዴ በተለይ በመሶብ፣ ሙዳይ እና ቃጤ የስፌት ዓይነቶች ላይ በአመዛኙ ጥቅም ላይ ይውላል።

ከምክንያታዊነት ስልት አንጻር በስፌት በዋናነት የሚጠቀሱት ግብዓቶችና መሥሪያ መሣሪያዎች ናቸው። ግብዓቶቹ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተፈጥሮአዊ መካከል የተክል ዓይነቶች፣ ማዕድናት እና የአየር ንብረት ሁኔታዎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ከመሥሪያ መሣሪያ እና ግብዓት መካከል ስንደዶ፣ ሰበዝ፣ ወይራ፣ ወርሳቢሳ እና ግራዋ ተፈላጊ እና ተመራጭ መሆናቸው፣ እንዲሁም አዎንታዊ እሳቤ መያዛቸው ከተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው የመነጨ ምክንያታዊ መነሻ ነው። የፀሐይ የድርቀት እና የመቀት መነሻ መሆን፣ እንዲሁም የውሃ የእርጥብነት መነሻ ከተፈጥሮአዊ ባህሪ ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱ ምክንያታዊነት ነው። የብረት የጠንካራነት እሳቤ መያዝ፣ የአመድ በምረት ሂደት ጥቅም ላይ መዋል፣ ከማዕድናቱ ተፈጥሮአዊ ስሪት ጋር የተያያዘ ነው።

ከወስፌ ስፌት ጋር ግንኙነት ያላቸው የፍካሬ ልቦና ጉዳዮች ሁለት ምድብ የታዩ ሲሆን፣ እነሱም የፍሮይድ የሰብዕና መዋቅሮች እና መንስኤዎች ናቸው። የሰብዓና መዋቅሮቹም ኢድ፣ ኢጎ እና ልዕለኢጎ ናቸው።

በኢድ የሰብዕና መዋቅር ሥነ ህይወታዊ ጉዳዮች፣ ግላዊነት ያላቸው አስተሳሰቦች፣ ፈጠራዊ ጉዳዮች፣ ግላዊ መሻቶች፣ ህልሞች፣ ተቀባይነት የሌላቸው ሩካቤያዊ እሳቤዎች፣ እንደግል ጥሩና መጥፎ ሊባሉ የሚችሉ ንግግሮችና ድርጊቶች በዚህ ሰብዕና ስር ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው።

በኢጎ መዋቅር የተለያዩ እውነታ ተኮር እሳቤዎች፣ ግላዊ ጉዳዮች፣ መንስኤዎች እና ሚዛናዊ የሆኑ ነጥቦች ይጠቀሳሉ። በግላዊና በማኅበራዊ ጉዳዮች መካከል የሚስተዋሉ ሥነልቦናዊ ጉዳዮች፣ ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች ሚዛን እንዲጠብቁ የሚደረጉት በኢጎ የሰብዕና መዋቅር ነው። ለዚህ

ማሳያም በሥነቃላዊ ጉዳዮች ዘንድ ያሉ ጭንቀቶች፣ እፍረቶች፣ በክልከላ ንግግሮች የሚጠቀሱት ምክንያቶች እና ሚዛናዊ እሳቤዎች በዚህ አግባብ የታዩ ናቸው።

በመጨረሻም የሚጠቀሰው የሰብዕና መዋቅር ልዕለኢጎ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ማኅበረሰባዊ እና ግብረገባዊ ጉዳዮች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። በዚህም በማኅበረሰቡ ቅቡልነት ያላቸው እሳቤዎች እና ሞራላዊ ድርጊቶች ይጠቀሳሉ። በማኅበረሰብ ደረጃ የሚስተዋሉ ማኅበረ-ባህላዊ ክንውኖች፣ ደንቦች፣ ስምምነቶች እና ክልከላዎች በዚህ አግባብ በማሳያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በዚህ የሰብዕና መዋቅር አንድ ጉዳይ ጥሩ ወይም መጥፎ ሊባል የሚችለው ከወል እይታ አኳያ ነው። በአንጻሩ ግላዊ ጉዳዮች በአመዛኙ ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም።

በግልም ሆነ በማኅበረሰብ ደረጃ ሊከሰቱ ለሚችሉ ሰብዕናዊ መዋቅሮች ሦስት መንስኤዎች ይጠቀሳሉ። እነዚህም አካባቢያዊ፣ ውልደታዊ እና የሁለቱ ቅንጅቶች ናቸው። ከአካባቢያዊ መንስኤዎች አኳያ በሙያዎቹ የሚስተዋሉ የስራ ክፍፍሎች፣ የግብዓት አጠቃቀም፣ የምርት አጠቃቀም፣ የሙያተኛ ምንነት እና ሌሎች ጉዳዮች የሚጠቀሱ ናቸው። በግብዓት ስንደዶና አክርማ የደጋ አካባቢ ግብዓቶች መሆን፣ የወንጋ ግብዓቶች የቆላ አካባቢ ግብዓት ማሳያነት ይጠቀሳሉ።

ከውልደትና ተፈጥሯዊ ከሆኑ ጉዳዮች አኳያ ደግሞ በሙያዎቹ ወንድነት ከጥንካሬ ጋር በተያያዘ ሲገለጽ ሴትነት ደግሞ ከውበታዊ እና ከትዕግስታዊ ጋር በተገናኘ ተገልጸዋል። ከአካባቢያዊና ከውልደታዊ ጉዳዮች አኳያ በማኅበተሰቡ የሚስተዋሉት የአመጋገብ ሁኔታ፣ አውድ፣ የእጅ ትኩሳት፣ እጅን ዓመድ መቀባት፣ የእውቀትና የልምድ ሁኔታዎች እና ከሙያዎቹ ጋር የተያያዙ የክልከላ ድርጊቶች በዚህ ረገድ የሚጠቀሱ ሰብናዊ መንስኤዎች ናቸው።

አንድ ማኅበረሰብ አዎንታዊ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ በቅድሚያ የማኅበረሰቡን አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ልማድ፣ ፍልስፍናና መሻቶች በጥናት ተለይተው ሊታወቁ ይገባል። ከጥናቱ ግኝት ለመገንዘብ እንደተቻለው ክልከላዎች እና ትምእርታዊ ጉዳዮች የአንድን ማኅበረሰብ ፍልስፍና፣ እምነት፣ ማንነትና ባህል የሚያሳዩ ናቸው። በዚህም ትምእርታዊ ጉዳዮች ሥነምግባርን፣ መቻቻልና የመተሳሰብ ሚና ያላቸው በመሆኑ የትምህርት ተቋማት በግብረ ገብ እና በሥነምግባር ሥርዓተ ትምህርቶች የሚካተቱበት አጋጣሚ ቢኖር።

በባህል ዘርፍ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ተመራማሪዎችና ተቋማት የተለያዩ ሥነቃላዊ ጉዳዮችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በመሰነድ አዎንታዊና አሉታዊ ሚና ያላቸውን በመለየት አዎንታዊ የሆኑትን የሚጠናከሩበትና ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚደረጉበት፣ አሉታዊ የሆኑት ደግሞ በሂደት ማኅበረሰቡን ባማከለ መልኩ በሌሎች መሰል ጠቃሚ ሥነ ቃሎች የሚተኩበትን ሁኔታዎች እና ለተጠቃሚው ማኅበረሰብ የሚደርሱበት አግባብ ቢፈጠር የሚሉት በጥናቱ በመፍትሄ ሃሳብነት የተነሱ ምክረሃሳቦች ናቸው።

በመጨረሻም በጥናቱ ወቅት ለማስተዋል እንደተቻለው የሥነቃላዊ ጉዳዮች እና ለውጥና ቀጣይነት፣ ማንነት፣ የሥርጸት እሳቤ፣ ጾታ ተኮር እና ሌሎች መሰል ንጽጽራዊ ጥናቶች ላይ ሌሎች አጥኚዎች በቀጣይነት የምርምር ጭብጥ ሊያደርጓቸው እንደሚችሉ በአጥኚው የቀረቡ የምርምር ነጥቦች ናቸው።

## ዋቢዎች


የቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፤ (2012)፤ የቦረና ወረዳ የሰርግ ሥነ ቃሎች ሰነድ (ያልታተመ ጥራዝ)።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ (1962)፤ *መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ (1993)፤ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፤

ደቡብ ወሎ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፤ (2011)፤ *ድንግል ውበት*፤ ደሴ፣ ስካይ ማተሚያ ቤት።

Ahmed Zekaria. (1999) Harari Basketry through the Eyes of Amina Ismael Sherif. In R. Silverman (Ed.), *Ethiopian Traditions of Creativity* (Pp. 47-63). Hong Kong: University of Washington Press.

American Psychological Association. (2010). *Publication Manual of the American Psychological Association* (6th ed.). USA: APA.

Bell, C. (1997). *Ritual: Perspective and Dimensions*. Oxford: Oxford University Press.

Berger, A. (2004). *Three Aspect of Signs*. Semiotic Analysis. Retrieved from http://pdfs.semiotic scholar.org.

Bronner, J. S. (Ed.). (2007). *The Analytical Essay of Alan Dundes: Metafolklore and Oral Literature Criticism*. In A.Dundes, Meaning of Folklore (pp. 77-87). University Press of Colorado, Utah State University Press. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/

Buszek, M. (2011). "Labor is My Medium": Some Perspective (s) on Contemporary Craft. *Archives of American Art Journal*, *Vol*. 50, No. (¾) pp. 66-75. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/23355888.

Danesi, M. (Ed.). (2004). *Messages, Signs, and Meaning: A Basic Textbook in Semiotic and Communication Theory* (3rd Ed.). Toronto, Ontario: Canadian Scholarship's Press.

Das, A.K. (1979). *Tribal Art and Craft*. Delhi, Agam.

Dorson, R. (1963). Current Folklore Theory. *Journal of Current Anthropology*. 4 (1), pp. 93-112.

Dorson, R. (Ed.). (1972). *Folklore and Folk Life: An Introduction*. Chicago, the University of Chicago Press.

Guerin, W., Labor, E., Morgan, L., Reesman, J., & Willingham, J. (2005). *A Handbook of Critical Approaches to Literature* (5th Ed). New York: Oxford University Press.

Hebbar, S. (2015). Exploring Basket Weaving Techniques for Space Making Elements through Computation Tools. International Master of Interior Architecture and Design. Faculty of Design. CEPT University.

Hornby, S.A. (2010). *Oxford Advanced Learner's Dictionary* (8th Ed.). Oxford: New York, Oxford University Press.

Johnson, R. (2010). Craft Knowledge of Disciplinarity in Writing Studies. *College Compositionand Communication, Vol*. 61, No. (4). pp. 673-690. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/27917868

Leinhardt, G. (1990). Capturing Craft Knowledge in Teaching. *Educational Researcher*, *Vol*. 19, No. (2). Pp. 18-25. Retrieve from http://www.jstor.org/stable/1176598.

Martin, B. & Ringham, F. (2000). *Dictionary of Semiotics*. London: Biddles.

McGee, R.J. & Warms, R.L. (2012). *Anthropological Theory an Introductory History* (5th ed.). USA: McGraw-Hill.

Moses, M. (2014). The Contribition of Indigenous Knowledge Use on the Livelihood of Rural Women in the Lowyeld Region of Swaziland: A Case Study of Handicrafts. (Mastre's thesis). University of South Africa.

Osei-Poku, P. & J. Osei. (2014). Production of on Loom Basketry Using Selected Local Material. *International Journal of Fiber and Textile Research*. Universal Research Publication. Retrieved on http//: www.urpjournal.com.

Quimby, L. G. (1976). Rev. of "Symbols and Society in Muslim Africa." *ASA Review of Books Publication Info.* Vol. 2: 163-174 pp. URL: http://www.jstor.org/stable/.

Sellschop, S., Goldblatt, W. & Hemp, D. (2005). *Craft South Africa*. Pietermaritzburg: Pan MacMillan SA.

Shanks, M. & McGuire, R. (1996). The Craft of Achaeology. *American Antiquity*. *Vol*. 61. No. (1). Pp 75-88. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/282303.

Silva, S. (2004). *Basketry: Africa*. Research Gate. Retrieved on http://www.researchgate.het /publication/281445436.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today: a User-Friendly Guide* (2nd ed.). New York and London, Routledge.

Witting, A. (2001). *Introduction to Psychology* (2nd ed.). Ball State University, McGraw-Hill Compenies.

Woodward, L. (2007). *Understanding Material Culture.* London: Saga Publication.